አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለ ግንኙነት (በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን)

በ
አሸቱ ወንድሙ

ሰኔ 1997 ዓ.ም
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለ ግንኙነት
# (በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን)

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር (Te Am)
ኤም.ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ
እሸቴ ወንድሙ

ሰኔ 1997 ዓ.ም
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት


**ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለው ግንኙነት (በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን)**


በ

እሸቱ ወንድሙ


## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

............................ ............................

አማካሪ ፊርማ

............................ ............................

ፈታኝ ፊርማ

............................ ............................

ፈታኝ ፊርማ

# ማውጫ


ምስጋና ---------- i

አህፅሮተ ጥናት ---------- ii

ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------- 1

1.2 የጥናቱ አላማ ---------- 4

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ---------- 5

1.4 የጥናቱ ወሰን ---------- 5

1.5 የጥናቱ ውስንነት ---------- 6

1.6 የቁልፍ ቃላት ሀሳብ መፍቻ ---------- 6

ምዕራፍ ሁለት፡ ክለሳ ድርሳን

2.1 የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዳራና አሁን ያለበት ሁኔታ ---------- 9

2.1.1 ጠቅላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምርት ዓላማ ---------- 9

2.1.2 የአማርኛ ቋንቋ እንደ ትምህርት አይነት ---------- 9

2.1.3 አማርኛ እንደ ማስተማርያ ቋንቋ ---------- 10

2.1.4 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የትምህርት ፖሊሲ አማርኛ ቋንቋን አስመልክቶ ያወጣቸው ድንጋጌዎች ---------- 11

2.2 ሥነ ትምህርታዊ ስነልቦና ---------- 12

2.3 ፍላጎት ምንድን ነው ---------- 13

2.4 ፍላጎትና የሁለተኛ የቋንቋ ትምህርት ---------- 15

2.4.1 የፍላጎት ጠቀሜታ ---------- 17

2.4.2 ፍላጎትና በትምህርት ውስጥ ያለው ሚና ---------- 17

2.4.3 ፍላጎትን ማጥናት ለምን ያስፈልጋል? ---------- 19

2.4.4 የተማሪዎችን ፍላጎት የማወቅያ ዘዴዎችና መንገዶች ---------- 21

2.4.5 ፍላጎት መመዘኛ ---------- 24

2.4.6 የሥራ መስኮች ትምህርት አይነት ፍላጎት ቅኝት ---------- 25

2.4.7 ፍላጎትና ሥርአተ ትምህርት ---------- 27

2.4.8 በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ---------- 28

2.4.8.1 ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና ግምት ---------------- 28
2.4.8.2 የመምህሩ የማስተማር ዘዴ ---------------- 30
2.4.8.3 የመምህሩ ስብእና ---------------- 32
2.4.8.4 ተማሪዎች አንድን ተግባር ለማከናወን ያላቸው ተነሳሽነት ---------------- 34
2.4.8.5 ማገሪው የሚገኝበት ሁኔታና ማህበራዊ ጉዳይ ---------------- 34
2.5 የቋንቋ ትምህርት ለመማር በጾታ መካከል ያለ ፍላጎት ልዩነት ---------------- 36
2.6 የትምህርት ውጤት ---------------- 38
2.6.1 በትምህርት ውጤት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ---------------- 39
2.6.1.1 ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት ---------------- 39
2.6.1.2 የማስተማር ዘዴ 40
2.7 ተማሪዎች አንድን ትምህርት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና
በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከል ያለው ዝምድና ---------------- 41
ምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ዘዴ
3.1 የቦታን አመራረጥ ---------------- 43
3.2 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ---------------- 43
3.3 በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ተጠኝዎች ---------------- 44
3.3.1 ተጠኝዎች ---------------- 44
3.3.2 የናሙና አወሳሰድ ---------------- 44
3.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ---------------- 44
3.4.1 የጽሑፍ መጠይቅ ---------------- 44
3.4.2 የተማሪዎችን ውጤት ---------------- 45
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ---------------- 46
ምዕራፍ አራት የመረጃዎች ትንታኔና ውጤት
4.1 የተጠያቂዎች አጠቃላይ ዳራ ---------------- 48
4.1.1 ፆታ ---------------- 48
4.1.2 ዕድሜ ---------------- 48
4.1.3 ከትምህርት ቤቱ የተወሰዱ ተማሪዎች ስብጥር ---------------- 49
4.1.4 ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚጠቀሙበት ቋንቋ ---------------- 49

4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ---------------------------49

4.2.1 በተማሪዎች ትምህርት ውጤትና ለትምህርቱ ባላቸው ፍላጎት መሃከል ያለው ግንኙነት ---------------------------49

4.2.2 በተማሪዎች ውጤትና ፍላጎት ከፆታ፣ ከትምህርት ቤት እና ከክፍል ደረጃ አንፃር ያለ ልዩነት ---------------------------51

4.2.2.1 በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል ያለ የትምህርት ውጤት ልዩነት ---------------------------51

4.2.2.2 በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር የሚታዩ ፍላጎት --------------------------- 52

4.2.3 በትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት ---------------------------54

4.2.3.1 በገብረጉራቻ ትምህርት ቤትና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት ---------------------------54

4.2.3.2 በፍቼ እና በትሐጽዮን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መሃከል ያለ የውጤት 55

4.2.3.3 በገብረጉራቻና በንሐጽዮን መሃከል ያለ የውጤት ---------------------------56

4.2.4 በትምህርት ቤት መሃከል ያለ የፍላጎት ልዩነት ---------------------------57

4.2.4.1 በገብረጉራቻና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል አማርኛ ቋንቋንለመማር የሚታይ ፍላጎት ---------------------------57

4.2.4.2 በፍቼና በንሐጽዮን መሃከል ያለ የፍላጎት ልዩነት ---------------------------58

4.2.4.3 በገብረጉራቻና በንሐጽዮን መሃከል ያለ የፍላጎት ልዩነት ---------------------------59

4.2.5 በየክፍል ደረጃ ያለ የፍላጎትና የውጤት ልዩነት ---------------------------60

4.2.5.1 9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት ---------------------------60

4.2.5.2 በ9ኛ ክፍልና በ10ኛ ክፍል መሃከል አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት ---------------------------61

4.2.6 ከትምህርት ቤቱ አንፃር ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው የአመለካከት ልዩነት --------------------------- 62

4.2.6.1 በገብረጉራቻ ትምህርት ቤትና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለው የአመለካከት ---------------------------62

4.2.6.2 በፍቼና በጎሐጽድን ትምህርት ቤት መሃከል ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው የአመለካከት ደረጃና ልዩነት ---------------------------------------- **64**

4.2.6.3 በገብረጉራቻና በጎሐጽዮን መሃከል ያለ የአመለካከት ደረጃና ልዩነት ---------------------------------------- 65

4.2.7 የማሪያዎች ውጤትና የትምህርት ፍላጎት ደረጃ ---------------------------------------- **66**

4.3 አጠቃላይ የውጤት ገለፃና ትንታኔ ---------------------------------------- 67

ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

5.1 ማጠቃለያና መደምደሚያ ---------------------------------------- 70

5.2 አስተያየት ---------------------------------------- 72

ዋቢ መጻሕፍት ---------------------------------------- **74**

አባሪዎች

መጠይቅ ........................................ i

የናሙናት መረጃ ........................................ iv

የውጤት መረጃ ........................................ vi

የትምህርት ቤት መረጃ ........................................ vi

የክፍል ደረጃ ........................................ vi

የጾታ መረጃ ........................................ vii

የእድሜ መረጃ ........................................ vii

አጠቃላይ መረጃ ዝርዝሮች ........................................ viii

የናሙናት ት/ቤትና አመለካከት መረጃ ........................................ viii

የናሙናት አመለካከትና ፆታ መረጃ ........................................ ix

የናሙናት አመለካከትና እድሜ መረጃ ........................................ x

የናሙናት፡ የአመለካከት እና የውጤት አማካኝ መረጃ ........................................ xi

የመረጃ መተንተኛ ቀመር ስሌት ........................................ xii

የፈተና አስተማማኝነት መለኪያ ቀመር ምሳሌ ........................................ xiv

የፒርሰን አስተማማኝ ደረጃን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........................................ xv

# የሠንጠረዥ ማውጫ


ገጽ

ሠንጠረዥ አንድ የተማሪዎች የፆታ ስብጥር፡፡ ....................48

ሠንጠረዥ ሁለት የተማሪዎችን እድሜ፡፡ ....................49

ሠንጠረዥ ሦስት፡ ከትምህርት ቤቱ የተወሰዱ ተማሪዎች ስብጥር ....................49

ሠንጠረዥ አራት፡ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ ባስመዘገቡት ውጤት መሃከል ያለው ዝምድና፡፡ ....................50

ሠንጠረዥ አምስት ፡ በሴትና በወንድ ተማሪዎች ውጤት መሃከል ያለ ልዩነት፡፡ ....................51

ሠንጠረዥ ስድስት፡ በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር የፍላጎት ልዩነት ....................53

ሠንጠረዥ ሰባት፡ ገብረጉራቻ ትምህርት ቤትና በፍቼ ትምህርተ ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነትን ....................54

ሠንጠረዥ ስምንት፡ በፍቼና በጉሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነትን ....................55

ሠንጠረዥ ዘጠኝ ፡ በገብረጉራቻና በጉሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነትን ....................56

ሠንጠረዥ አስር፡ በገብረጉራቻና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የአማርኛ ትምህርት ፍላጎት ልዩነት ....................58

ሠንጠረዥ አስራ አንድ፡ በፍቼና በጉሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የአማርኛ ትምህርት ፍላጎትን ....................59

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፡ በገብረጉራቻና በጉሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነትን ....................60

ሠንጠረዥ አስራ ሶስት፡ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት ....................61

ሠንጠረዥ አስራ አራት፡ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና ልዩነት ....................62

ሠንጠረዥ አስራ አምስት፡ በገብረጉራቻና በፍቼ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መሃከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለን የአመለካከት ልዩነት ....63

ሠንጠረዥ አስራ ስድስት፡ የፍቼና የጎሐጽዮን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መሃከል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን የአመለካከት ልዩነት ያሳያል። ....64

ሠንጠረዥ አስራ ሰባት፡ በገብረጉራቻና በጎሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል የአመለካከት ደረጃና ልዩነት ....65

ሠንጠረዥ አስራ ስምንት፡ ፍላጐትን እና ውጤትን በተመለከተ ከአማካይ በላይና በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች ---- 66

# ምስጋና

ለዚህ ጥናት መሣካት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝና የሥራዬን ሂደት በመከታተል በማቃናትና በማዳበር ለዚህ ደረጃ እንዲደርስ ላስቻሉት አማካሪዬ ዶ/ር ግርማ አውግቸው ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በማስከተልም በርዕስ መረጣ ወቅት ርእሴን በማቃናትና በማስተካከል እገዛ ላደረጉልኝ መምህሬ ለአለም እሸቱ (ረ/ፕሮፌሰር) ልዩ እገዛ በማድረግ፣ የተለያዩ አጋዥ መሣሪያዎችን በመጠቆምና አስተያየቶችን በመስጠት ላበረታቱኝ የሥነ ልቦና ምሁራን ለታምሬ እንዱአለም (ረ/ፕሮፌሰር) ና ለአቶ አበባው ምንአየ ፣ ጽሑፉን አርትኦት በማድረግ ለተባበረኝ ሙሃመድ ጀማል፣ ስራዬን በአግባቡ አጠናቅቅ ዘንድ ከላፕቶፕ ኮምፒውተር ጀምሮ ሙሉ እገዛው ላልተለየኝ ለአበበ ዘውዱ፣ እና በስራዬ ወቅት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እገዛ ላደርጉልኝ በሙሉ ከልብ የፈለቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# አህፅሮተ ጥናት (Abstract)


የዚህ ጥናት ዋና አላማ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ዝምድና መኖሩንና አለመኖሩን ማየት ነው፡፡ የጥናቱ አስፈላጊነት በውጤትና በፍላጎት መካከል ዝምድና መኖሩን እና አለመኖሩን በማረጋገጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት በአግባቡ መከናወን የሚችልበትን ምቹ መንገዶችን ማመላከቱ የጥናቱ አስፈላጊነት ነው፡፡ እንዲሁም በተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት ዙሪያ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ተላውጦዎችን ለማወቅ ሠፊ ጥናት ማከናወን እንዲቻል ይረዳል፡፡ ጥናቱንም ከግብ ማድረስ እንዲቻል የፍላጎት መመዘኛዎችም በተለያዩ ምሁራን ፅንሰሃሳብና መመሪያ መሰረትነት ተዘጋጅቷል፡፡ ጥናቱን ለማከናወን የሚረዱ ናሙናዎች ተወስደዋል፡፡

ጥናቱ የሚከናወነው በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ከሚገኙ አስራ አምስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሦስት ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶቹም በእጣ ንሞና የተመረጡ ናቸው፡፡ ከነዚህም ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሁለት መቶ አሥራ ስድስት ተማሪዎች ከዘጠነኛና ከአሥረኛ ክፍል ተወስደዋል፡፡

ከተማሪዎቹም የመማር ፍላጎት እና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት በመረጃነት ከተሰበሰበ በኋላ የመማር ፍላጎት አማካይ እና መደበኛ ልይይት፣ በቋንቋው ያስመዘገቡት የውጤት አማካኝ እና መደበኛ ልይይቱ ለብቻ ለብቻ እንደየ ርዕሠ ጉዳዩ ተሠርቶ ቀርቧል፡፡ አማካይና መደበኛ ልየነቱን መሠረት በማድረግም ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በቋንቋው ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት በፒርሠን የግንኙነት መለኪያ ቀመር ተሠልቶ ቀርቧል፡፡ ስሌቱም እንደሚያሳየው በውጤትና በፍላጎት መካከል አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት እንዳለ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ከፆታ፣ ከትምህርት ቤት እና ከክፍል ደረጃ አንፃር ልዩነት መኖሩን ለማየት የአማካይ ውጤት ልዩነትን መሠረት በማድረግ ታይቷል፡፡ በአማካይ መካከል ያለው ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የቲ - ቴስት ቀመርም ተግባር ላይ ውሏል፡፡ በዚህ መሠረት የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከፆታ አንፃር፣ በፍላጎትም ሆነ በውጤት፣ የጎላ ልዩነት ያለ መኖሩን፣ ከትምህርት ቤት አንፃር ደግሞ የፍላጎትም ሆነ የውጤት ልዩነት ያለመሆኑን እና ከክፍል ደረጃ አንፃር ሲታይ በውጤት የጎላ ልዩነት የሌለ ሲሆን ከፍላጎት አንፃር ግን ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም ከተገኘው ውጤት በመነሣት በቋንቋ ትምህርት ላይ ችግር ናቸው የተባሉትን በማስመልከት የመፍትሔ ሃሣቦች ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

# ምእራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ (Background of the study)

ቋንቋን በሚመለከት የሚከናወን ጥናት ወይም የሚሠነዘር ሃሳብ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሰውን ልጅ የህይወት ውጣ ውረድን፣ ማህበራዊ ጉዳይን እና ባህላዊ ዳራን ወዘተ የመሳሰሉትን መዳሰስ አይቀርም። ስለዚህም ነው ቋንቋ በማህበረሰብ ውስጥ የሚታዩትን የባህል፣ የአኗኗር፣ የአጠቃቀም ስርአት ወዘተ መግለጫ ነው የሚባለው (Hadson 1980; Stweart 1968, Mackey 1965; Stwart 1980)

ስለዚህ ቋንቋን በተሻሻለ መንገድ መጠቀም መቻል አስፈላጊና አቢይ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ለማህበረሰቡ በብቃት እዲያገለግልና ምቹ ሁኔታን ለማመቻቸት በዘርያው የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ ያስፈልጋል። በጥናት ላይ የተደገፈ አሰራርና የመማር ማስተማር ተግባር ደግሞ የተሳሳተውን አካሔድ ለማቃናት፣ ጠንካራ ጎኑን ለማበረታታት እና በተስተካከለ መንገድ ለማስኬድ ይረዳል። ስለዚህ የቋንቋ ትምህርት ለአፈ-ፈትና ለኢ-አፈፈት ተማሪዎች ሲሠጥ በጥናት የተደገፈ መረጃን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት። ይህን ለማከናወን ደግሞ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ሥሜት የጎሺ ሁኔታን፣ ባህላዊ ዳራን፣ አካባቢያዊ ተፅእኖን የእውቀት ደረጃን ወዘተ ማጤኑ ወሣኝ ጉዳይ ነው (Harmer 1991; Rubinsen 2001 and Skinner 1959) ከላይ ከተዘረዘሩት ተላውጦዎች ውስጥ ፍላጎት (Interest) በቋንቋ ትምህርትም ሆነ በሌላ ትምህርት ዙሪያ አቢይና መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የፍላጎት መኖር ወይም ያለመኖር ለአንድ ተግባር ስኬታማ መሆን ወይም ያለመሆን ወሳኝ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ፍላጎት ለትምህርት መሠረታዊ ጉዳይ ስለሆነ ከሌሎች ተላውጦዎች በተለየ መልኩ መጠናት አለበት በማለት Evans (1965) Skiners (1985) እና Bugleski (1971) ይገልፃሉ።

ቋንቋን በመማር ማስተማሩ ሂደት ወትት ያለ እንቅፋት እንዲካሄድ እና አጥጋቢ ውጤት እንዲመዘገብ ከተፈለገ ተማሪዎች ለትምህርቱ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል። የፍላጎት መኖር ለትምህርቱ ግብ መምታት ወሣኝ ጉዳይ ነው (Harmer 1991 and Evans1965)። በመሆኑም ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ ፍላጎት ካላቸው በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡና በአንፃሩ ደግሞ አሉታዊ ፍላጎት ካላቸው ውጤታቸው ዝቅ ከማለቱም

በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይም ችግር እንደሚፈጥር የተለያዩ ጥናቶች ያስረዳሉ (Skinner 1959)::

ፍላጎት እንደ አመለካከት፣ ዝንባሌ (Orentation) እና ንሺ (Motivation) ሁሉ በተማሪዎች ባህሪ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድር የሚጠቁሙ የተለያዩ መረጃዎች በተለያዩ ሊቃውንት ቀርበዋል (ለምሳሌ McCombs (1997); Tudor (1996); Bell (1970); Schonell (1961); Harmer (1991); Hancock (2001); and Bugelsk (1971) ይመልከቱ):: በተጨማሪም Harmers (1991) ፍላጎት የንሺ ዋነኛው አካል እንደሆነ ሲረጋ አይገባም በማለት የንሺ ሌላው አካል እንደሆነ ይገልፃል:: በዚህም ረገድ ብዙ የሥነልቦና ሊቃውንት ፍላጎት ከውስጣዊ ንሺ (Integrative motivation) ጋር ተመሣሣይ ከመሆኑም በላይ በተማሪዎች ውጤት ላይም የራሱ አስተዋጽኦ እንዳለው ይገልጻሉ::

ፍላጎት ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል:: ይሁን እንጂ የተማሪዎች ውጤት ከቦታ፣ከትምህርት ቤት፣ከጾታ አንፃር ሲታይ የተለያየ ሊሆን ይችላል:: ለዚህም ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ፖለቲካዊ፣ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ይጠቀሳሉ:: እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ:: ከዚህም የተነሳ ተማሪዎች በአንዳንድ ትምህርት ቤት ከፍተኛ በሌላ ትምህርት ቤት ደግሞ አነስተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ ይስተዋላል (Tudor1996; Skinner1985; Hurlock1980; and Grray1970)::

የተማሪዎች ፍላጎትና ውጤት ተዛምዶን በተመለከተ በተደረገው የመስክ ጥናት ወቅት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አንዳንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበው ታይተዋል:: ዝቅተኛ ውጤት ለማምጣታቸው ምክንያቱ ምን እደሆነ ለተማሪዎቹ ጥያቄ ቀርቦላቸው የሰጡት መልስ፣ ትምህርቱን የመማር ፍላጎት ስለሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል:: ይህ ሁኔታ ደግሞ የቋንቋው ሥርአተትምህርት ሲዘጋጅ የተማሪዎችን ፍላጎት ምን ያህል ከግምት አስገብቶአል የሚለው ጥያቄ አጥኚውን ለጥናቱ አነሳስቶታል::

ከዚህም በመነሳት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲማሩ ሲደረግ ተማሪዎቹ ስለ ቋንቋው ያላቸው ፍላጎት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ጥናት ማከናወን ያስፈልጋል:: ይሁን እንጂ በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅትም ጥናት መከናወኑን እና አለመከናወኑን ለማየት ተሞክሮ ምንም ዓይነት መረጃ እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል::

የተለያዩ ሊቃውንት እንደሚገልፁት አንድ ስርዓተ ትምህርት በሚዘጋጅበት ወቅት ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ የተማሪዎቹን ፍላጎት መለካት እና ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው:: ይህም የሚያስፈልግበት አብይ ምክንያት የትምህርት ፕሮግራሞችን ለማሳደግ፣ ትክክለኛ

አላማን ለማዘጋጀት፣ ለትምህርቱ አመቺ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴ ለመምረጥ፣ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን አስቀድሞ ለመከላከል፣ የተማሪዎችን ፍላጎት በተመለከተ የተለያዩ ትምህርታዊ ምርምሮችን ለማከናወን፣ የፈተና ፕሮግራሞችን ለማውጣት እና የሚዘጋጀው ትምህርት ከተማሪዎቹ ዝንባሌና ፍላጎት ጋር ለማጣጣም ይጠቅማል በማለት Bickley (1990); Bugleski (1971) Craig (1979) ይገልጻሉ::

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እየተሰራበት ያለውን የትምህርት ሥርአት ስንመለከት፣ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የትምህርት ፖሊሲ አማርኛ ቋንቋን አስመልክቶ በ1986 ዓ/ም ላይ በቁጥር 3.5.3 ያወጣው ድንጋጌ የአማርኛ ቋንቋ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ግንኙነት ያገለግል ዘንድ በትምህርትነት ይሰጣል ይላል:: በማስታወቂያ ሚኒስቴርም የፐሬስና የኦዲቪዥዋል መምሪያ (1994፤62) ባዘጋጀው መፅሔት ላይ የአማርኛ ቋንቋን በተመለከተ እንደሚከተለው ሰፍሯል::

> *ተማሪዎች የፌደራል መንግስት የሥራ ቋንቋ የሆነውን አማርኛ እንዲማሩ ይደረጋል:: ክልሎችም ይህን ተረድተው አማርኛን ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ እንዲማሩት መረዳት ይገባቸዋል:: ፖሊሲው ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ መብት ቢሠጥም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አማርኛ ቋንቋን እንዲማር የሚያደርግ ነው:: ስለዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ በተወካዮቹ አማካኝነት የወሰነውን በህገ መንግስቱ ውስጥ እዲሰፍር የተደረገ በመሆኑ ተማሪው የአማርኛ ቋንቋን የመማር ግዴታ እንደሚኖርበት የሚያሣውቅ ነው::*

ይሁን እንጂ በ1986 ዓ/ም በትምህርት ሚኒስቴር የወጣውን መመሪያ ስናይና በአሁኑ ወቅት እየተሰራበት ያለውን የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ ደግሞ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝቅተኛ ደረጃ ተሰጥቶት እናገኛለን:: ለአብነትም ያህል:-

- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለአፈ.ፈት ተማሪዎች ከ1-12ኛ ክፍል ፤ለኢ-አፈ.ፈት ደግሞ ከ1-10ኛ ክፍል እንደ አንድ የትምህርትነት ዓይነት እንዲሠጥ የተወሰነ ሲሆን ፤ ለኢ-አፈ.ፈት ደግሞ ከ11ኛ-12ኛ ክፍል ከክልሉ ቋንቋ ወይም ከአማርኛ በአማራጭነት እንዲማሩት ተወስኗል::

- የመሠናዶ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለመግባት ከሚወስዱት ፈተና ውስጥ አማርኛ አልተካተተም::

ያሁንና ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፤ለኢ-አፈ.ፈት ከ3ኛ ክፍል የምር እንዲሰጥ ቢገለጽም በኦሮሚያ ክልል ግን ከ5ኛ ክፍል ነው የሚጀምረው:: ይህም ደግሞ

የትምህርት ሚኒስቴር አማርኛ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ በትምህርትነት እንዲሰጥ ካወጣው ድንጋጌ ውጭ ከመሆኑም በላይ ተማሪዎች ለትምህርቱ በሚኖራቸው ግባት ላይም ተጽእኖ ማሳደሩ እንደማይቀር ይገመታል።በሌላም በኩል ከመሠናዶ ትምህርት በኋላም ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ከሚሠጡት ፈተናዎች ውስጥም የአማርኛ ቋንቋ አልተካተተም። ይህም ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት ሊቀንስ ይችላል።

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ጉዳዮች አነሳሽነት አጥኚው በኦሮሚያ ክልል የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ፍላጎትና የውጤት ተዛምዶ መመርመርን አላማ አድርጎ ተነስቷል። ከዚህም በተጨማሪ፡-

1. በድሮውም ሆነ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ዝግጅት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ፍላጎት የሚዳስስ ጥናት አለመካሄዱ፣
2. አማርኛ ወደከፍተኛ የትምህርት ተቋም መግቢያነት እንደ ሌሎቹ የትምህርት አይነቶች ማያካተት መቅረቱ፣
3. የአማርኛ ቋንቋ በኦሮሚያ ክልል ከ5ኛ ክፍል መጀመሩ እና፣
4. የኦሮሚያ ክልል የሥራ ቋንቋ ኦሮምኛ በመሆኑ ምክንያት ተማሪዎች
   - የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን ይመስላል?
   - በአማርኛ ቋንቋ የሚያስመዘግቡት ውጤትስ ምን ይመስላል?
   - ቋንቋውን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መካከልስ ምን ግንኙነት ይኖራል? እና

የሚሉትን መሪ ጥያቄዎች ለዚህ ጥናት እንደ መነሻ ምክንያቶች ሆነዋል።

## 1.2 የጥናቱ አላማ (Objective of the Study)

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማ፣ ፍላጎት የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽእኖ ለማየትና በተማሪዎች ፍላጎትና ውጤት መሐከል ያለውን ግንኙነት ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። በዚህም ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮችን ለመመለስ ይሞክራል፣

1. ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል ማረጋገጥ፣
2. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስመዘግቡት ውጤት ምን እንደሚመስል ማረጋገጥ፣
3. ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ በሚያስመዘገቡት ውጤት መካከል ያለውን ዝምድና (ግንኙነት) ማወቅና ማረጋገጥ እና
4. በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ ከሚያስመዘገቡት ውጤት መካከል ያታዊ ልዩነት መኖሩን ማረጋገጥ ናቸው።

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት (Significance of the Study)

ቋንቋን ለመማር ስንነሳ የመማር ፍላጎት የመኖር ጉዳይ ወሣኝ ነው:: ፍላጎት ደግሞ ብቻውን የሚገኝ ሳይሆን ከሌሎች የሥነልቦና ክፍሎች ለምሳሌ ከአመለካከት፣ ከንሺ፣ ከዝንባሌ፣ ከትኩረት፣ ከስሜትና ከመሣሠሉት ጋር ተያያዥነት ያለው ነው (Skinner1985: Bugleski1971):: እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ተላውጦዎችም የጥናቱን ውጤት ፈርጅ ብዙ ያደርጉታል:: የአማርኛ ቋንቋ የፌደራልና የሃገሪቱ የመግባቢያ ቋንቋ ስለሆነ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ይግባባበታል:: በትምህርት ቤቶችም አማርኛ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ቋንቋነት ይሰጣል:: አንድን ቋንቋ ለመማር ደግሞ ፍላጎት ዋንኛውና አስፈላጊ ነው:: በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል::

1. ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ያላቸውን የፍላጎት ደረጃ ያሳያል::

2. መምህራን የማስተማር ዘዴያቸውን ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አጣጥመው እንዲያቀርቡ መረጃ ይሰጣል::

3. ከጾታ አንፃር ትምህርቱን ለመማር የትኞቹ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው በማሳየት ዝቅተኛ ፍላጎት ያላቸውን በመለየት ልዩ እገዛና ማነቃቂያ መስጠት እንዲቻል ይረዳል::

4. ለመርሃ ትምህርትና መርጃ መሳሪያ አዘጋጆች የመነሻ ሃሳብ ይሠጣል::

5. ወደፊት በተመሳሳይ ርእስ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኚዎች ፍንጭ ይሰጣል::

## 1.4 የጥናቱ ወሰን (Delimitation of the Study)

ጥናቱ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በሙሉ አላጠቃለለም:: በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ካሉት 16 ዞኖች መካከል ሰሜን ሸዋ ዞን ምክንያታዊ ንሞና (Purposive sampling) አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል:: ስለዚህ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት በሰሜን ሸዋ ዞን ስር የሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ናቸው:: ከሰሜን ሸዋ ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሰረት 15 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይገኛሉ:: ከነዚህ ትምህርት ቤቶች መካከል ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በነሲብ ንሞና መሰረት ተመርጠዋል:: ከትምህርት ቤቶችም ውስጥ የተወሰኑ ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል::

በሌላ በኩል በኦሮሚያ ክልል በአማርኛ ቋንቋ ኢአፈፊት የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ውስጥ በነሲብ ንሞና ተመርጠው ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ፍላጎት

ከውጤታቸው ጋር የሚያነፃፅር ነው:: በመሆኑም በሰሜን ሸዋ ዞን ከሚማሩት ተማሪዎች ውስጥ ኢ-አፈፊት ተማሪዎች ብቻ ተካተዋል:: ምክንያቱም ኢአፈፊት ተማሪዎችን መሰረት ያደረገ ጥናት ስለሆነ ነው:: በዞኑ ውስጥ በአማርኛ አፈፊት የሆኑት በጣም ጥቂት ስለሆኑ እንዳይካተቱ ተደርገዋል::

## 1.5 የጥናቱ ውሱንነት (Limitation of the Study)

በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ያሉ የመሰናዶ ተማሪዎችን በጥናቱ ውስጥ ለማካተት ተሞክሮ ነበር ሆኖም በሦስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር የመረጡ ተማሪዎች ከ አስር አይበልጡም:: ትምህርቱንም የመረጡ ተማሪዎች አብዛኞዎቹ በአማርኛ ቋንቋ አፈፊት የሆኑ ናቸው:: ኢአፈፊት የሆኑ ተማሪዎች በጣም ጥቂት ስለሆኑ እና አማራጭ መንገድ ስለጠፋ የመሰናዶ ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተዋል:: በጥናቱ ውስጥ እንደ ውስንነት ይታያሉ:: በሌላ በኩል በናሙናነት ከገብረ ጉራቻ ት/ቤት የተወሰዱት ተማሪዎች 72 ሲሆኑ በመጠይቅ አሞላል ጊዜ በተከሰተ ስህተት የ10 ተማሪዎች መጠይቅ የተሳሳተ አሞላልን ስለተከተለ አስሩ ተማሪዎች ከጥናቱ ውስጥ እንዲቀሩ ተደርጓል::

## 1.6 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት መፍቻ

ሁለተኛ ቋንቋ ........................................................Second language
ሃይል ........................................................ Reinforcement
መርሳት ........................................................ Lapsing
መደበቅ ........................................................ disguised
ሚና መጫወት ........................................................ Role playing
ማስተማር ........................................................Teaching
ምላሽ ........................................................ Response
ምክንያታዊውንምና........................................................Purposive sampling
ምኞት ........................................................ Ambitions
ሥነ ትምህርታዊ ሥነ-ልቦና ........................................ Educational Psychology
ሥርአተ ትምህርት ........................................................ Curriculum
ሥነ ትምህርት ........................................................ Education
ሥነ ልቦና ........................................................ Psychology
ስብዕና ........................................................ Personality
ስፍርታዊ ገሺ ........................................................ Instrumental motivation
ሥፍረታዊ ዝንባለ........................................................ Instrumental orientation

ስሜት ........................................................ Feeling

ስሜታዊ ........................................................ Affective

ስጦታ ተሰጥኦ ........................................................ Aptitudes

ተላውጦ ........................................................ Variables

ተስተምህሮ (ትምህርት) ........................................ Learning

ተግባር ........................................................ Action

ታታሪነት ........................................................ Interprising

ትንቢት ........................................................ Prophecy

ትኩረት ማስተዋል ............................................ Concentration

ንሸ ........................................................ Motivation

አለኝታ (ተስፋ) ............................................ Hopes

አላባውያን ........................................................ Elements

አስጊ ደረጃ (ዋጋ). ............................................ Critical value

አመለካከት ........................................................Attitude

አእምሮአዊ ........................................................ Cognitive

ከልብ ፡ የሚከታተል ............................................ Attention

ክንውን ........................................................ Success

ውህዳዊነት ........................................................Integrativeness

ውህዳዊ ንሸ (ውስጣዊ ንሸ). ................................ Integrative motivation

ውህዳዊ ዝንባሌ (ውስጣዊ ዝንባሌ).........................Intergrative orientation

ውስጣዊ ዝንባሌ ............................................ Instrumental orientation

ውጤት ስኬት........................................................Achievement

የሚግባባ (ግልጽ የሆነ) ................................ Exterovertion

የማወቅ ፍላጎት ............................................ Curiousity

የማይግባባ (ዝምተኛ) ................................ Extrovertion

የትምህርት ውጤት ............................................ Academic Achievement

የአፍ መፍቻ ቋንቋ............................................ first language

የስብእና መመዘኛ (መለኪያ) ................................ Personality Inventory

የፍላጎት መመዘኛ (መለኪያ) ................................Interest Inventory

የንሸ ባህሪያት ............................................ Motivational behaviour

የመማር ስልት ............................................ Learning style

የአስተማማኝነት ደረጃ ....................................Level of significance

(significant level)

የደረጃ ነፃነት ..........................................................Degree of freedom

ጉጉት ............................................................................ Curiousity

ግንኙነት ....................................................................... Correlation

ፈላጊ ..............................................................................Desirable

ፍላጎት ......................................................................... Interest

# ምራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

## 2.1 የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዳራና አሁን ያለበት ሁኔታ

### 2.1.1 አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ትምርት ዓላማ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማርኛ ቋንቋ የፌደራል ቋንቋ ስለሆነና ክልሎች ከክልሎች ጋር ወይም ከፌደራል መንግስት ጋር፣ ብሔረሰብ ከብሔረሰብ ጋር በመግባባት ችግራቸውን እንዲፈቱ አንድ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ ተማሪዎች አማርኛን በትምህርት ቤት መማር እንዳለባቸው ነው። በዓላማውም መሰረት የትምህርት ሚኒስቴር በተለያዩ የክፍል ደረጃ ለአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ቀርፆለት ትምህርቱ በመስጠት ላይ ነው። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት ባወጣው መግለጫ መሰረት በቁጥር 2.2.1.2 ብሔር ብሔረሰቦች የአማርኛ ቋንቋን በመናገር ከፌደራል መንግስትና ከክልል ማህበረሰብ ጋር መግባባት እዲችሉ ማድረግ ነው።

### 2.1.2 የአማርኛ ቋንቋ እንደ ትምህርት አይነት

የአማርኛ ቋንቋ እንደ ትምህርት አይነት መስጠት የጀመረበትን ጊዜ ለማወቅ በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ ስራዎች፣ የቀረቡትን ሀሳቦችና መረጃዎች መሰረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ ለማቅረብ ተሞክሯል።

ሩፊኖ ተፈራ (1991)፣ Pubnkhourst (1976) እና የኢሕዲሪ የትምርት ፖሊሲ ጥራዝ አንድ (1981) እንዳስረዱት ዘመናዊ ትምህርት በሀገራችን የተጀመረው 1900 ዓ.ም አካባቢ ነው። አማርኛ ቋንቋ በዚህ ወቅት የመንግስትና ኦፊሴላዊ ቋንቋ ነበር። ትምህርት በፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚሰጥ ሲሆን አማርኛ፣ አረብኛ፣ ጣልያንኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጡ ነበር።

በንጉስ ሃይለ ሥላሴ ዘመንም እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ አማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል። ነገር ግን ጣልያን በ1928 ከመጣ በኋላ ከፋፍለህ ግዛው በሚለው እሳቤ ኢትዮጵያን በስድስት አስተዳደር ክልሎች በመከፋፈል ትግርኛ በኤርትራ አካባቢ፣ አማርኛ በአማራው አካባቢ፣ አማርኛና ኦሮምኛ በአዲስ አበባ አካባቢ፣ ሱማልኛ በሱማሌ አካባቢ . . . በማስተማርያ ቋንቋነትና እንደ ትምህርት አይነት ተሠጥቷል። ከጣልያን ወረራ በኋላ እስከ 1986 ዓ.ም ድረስም እንደ አንድ የትምህርት አይነትነት ሲሰጥ ቆይቷል።

በ1986 ዓ.ም የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ መተግበር እስከ ጀመረበት 1987 ዓ.ም ድረስ አማርኛ በመላው ሀገሪቱ ውስጥ ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች በትምህርትነት ይሰጥ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የትምህርቱ ፖሊሲ በተግባር ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ ግን ቋንቋው እንደ ትምህርት አይነት የመሰጠቱ ሁኔታ ከክልል ክልል ተለያይቷል፡፡

በአማራው ክልል፣ በአዲስ አበባ መስተዳደር፣ በድሬድዋ ካውንስል፣ በቤኒሻንጉል ክልል፣ በአፋር ክልል የአማርኛ ቋንቋ ከ1ኛ - 12ኛ ክፍል እንደ አንድ የትምህርት አይነት በመሰጠት ላይም ነው፡፡ እንዲሁም በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ የማስተማሪያ ቋንቋቸው አማርኛ ለሆኑት ከ1ኛ-12ኛ ክፍል እንደ አንድ ቋንቋ ይሰጣል፡፡

በሌላ በኩል አማርኛ ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ላልሆኑት ክልሎች ከኦሮሚያ ክልል በስተቀር ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ በትምህርት አይነትነት የሚሰጥ ሲሆን፣ ለመሰናዶ ትምህርት ሲደርስ ከክልሉ ቋንቋ ጋር እንደ አማራጭ ይቀርባል፡፡

በኦሮሚያ ክልል ደግሞ ትምህርቱ እንደ አንድ የትምህርት አይነት መሰጠት የሚጀምረው ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ይዘልቃል፡፡ ለመሰናዶ ተማሪዎች ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ላልሆኑት ክልሎች ሁሉ ቋንቋው ከክልሉ ቋንቋ ጋር በአማራጭነት በማቅረብ ቋንቋውን የመረጡት ተማሪዎች ብቻ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይማሩታል፡፡

የክፍለ ጊዜው ስርጭትም በትምህርት ደረጃና ከክልል ክልል የሚለያይ ሲሆን ከ3ኛ-8ኛ ክፍል ድረስ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑት የተመደበለት ክፍል ጊዜ በሳምንት ከ3-5 ክፍለ ጊዜን ይይዛል፡፡ ከ9ኛ-10ኛ ክፍል ደግሞ ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ በሳምንት ተመድቦለት እንደ አንድ የትምህርት አይነት በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡

### 2.1.3 አማርኛ- እንደ ማስተማርያ ቋንቋ

ሃረዶ (1991)፣ የማስታወቅያ ሚኒስቴር (1994)፣ ሙሉመቤት (1989) እና የትምህርት ስልጠና ፖሊስ ጥረዝ አንድ (1981) መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ ትምህርት መሠጠት የተመረው ከ1900 አካባቢ ጀምሮ እንደነበረና በዚህ ወቅት የማስተማሪያ ቋንቋ የነበረው ፈረንሳይኛ ቋንቋ ነበር፡፡ በኢጣልያን ወረራ ወቅት የነበረው ደግሞ ከፋፍለህ ግዛ የሚለው መርህ መሰረት ለከፍፍሉ ዋንኛውና መሰረታዊ መመዘኛው ቋንቋ ነበር፡፡ በ1928 ጀምሮ የኢጣልያን ገዥ በስድስት (6) አስተዳደር ክፍሎች በመከፋፈሉ ምክንያት አማርኛ ቋንቋ በአማራውና በአዲስ አበባ አካባቢ የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ነበር፡፡ ጣልያን ተሸንፎ ከኢትዮጵያ ከወጣ ከ1931-1956 ዓ.ም በኋላ ባለው የቋንቋ ፖሊስ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ በማስተማርያ ቋንቋነት ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ተወስኖ ይሰጥ ነበር፡፡ ከ1958/9 ጀምሮ አማርኛ ቋንቋ ከ1ኛ-6ኛ

ክፍሎች የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን ተደርጓል። ይህም በአዲሱ መንግስት የወጣው በ1986 ዓ.ም የወጣው የትምህርት ስልጣና ፖሊሲ መተግበር እስከ ጀመረበት 1987 ዓ/ም ድረስ በተግባር ላይ እየዋለ ይገኛል።

አዲሱ የትምርት ስልጠና ፖሊሲ መተግባር ከጀመረበት 1987 ዓ.ም ጀምሮ ግን ቀድሞ የነበረው ሂደት ተለውጧል። የኢፌድሪ መንግስት በ1986 በሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት ቋንቋን አስመልክቶ ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ ዝግጅት እያደረጉ እንዲያስተምሩ ስለተፈቀደ ክልሎች የራሳቸውን ቋንቋ ለማስተማርያነት እያዋሉ ናቸው።

ያሁን እንጂ በተወሰኑት ክልሎች በአማራው፣ በቤኒሻንጉል ከ1ኛ-8ኛ ክፍል፣ በአዲስ አበባ መስተዳደር፣ በድሬድዋና በአፋር ክልል ከ1ኛ-6ኛ ክፍል እና እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በሃረሪና በደቡብ ክልል በአንዳንድ ቦታዎች በክልሉ ቋንቋ ኢ-አፊፊት ለሆኑት አማርኛ ቋንቋ በማስተማሪያ ቋንቋነት በማገልገል ላይ ይገኛል።

## 2.1.4 የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት የትምህርት ፖሊሲ አማርኛ ቋንቋን አስመልክቶ ያወጣቸው ድንጋጌዎች

የኢፌዲሪ መንግስት በ1986 አገሪቱ የምትመራበትን የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ ሲያወጣ የአማርኛ ቋንቋን አስመልክቶ የሚከተሉትን ነጥቦች አስቀምጧል። «ቋንቋና ትምህርት» በሚለው አርእስት ስር የሰፈሩት ነጥቦች በቁጥር 3.5.2 ላይ ብሄር ብሄረሰቦች አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ በራሳቸው ቋንቋ ወይም በብሄራዊ ክልላዊና በሀገር ውስጥ ባላቸው የተናጋሪ ብዛት ደረጃ መሰረት በሚመርጡት ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል ይላል። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ክልሎችም ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ ለጋራ መግባቢያ የአማርኛ ቋንቋን በትምህርትነት እየተማሩት ይገኛሉ። ይህንን በተመለከተ በቁጥር 3.5.3 ላይ የወጣው መመሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ግንኙነት የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል። ትምህርቱ ቢሰጥም በየክልሎቹ ውስጥ ትምህርቱ የሚጀምረው በተለያዩ ክፍሎች ላይ ነው። ቢሆንም በስርአት ትምህርት ውስጥ አስገብተው እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ በመስጠት ላይ ይገኛል።

ከላይ በተጠቀሱት አንቀጾች ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች ስንመለከት ከምናገኘው ነጥብ በመነሳት ክልሎች ለትምህርትነት ከሚመርጡት ቋንቋ በተጨማሪ ከክልሉ ውጪ መግባባት እንዲቻል ሁሉንም ሊግባባ የሚችል አንድ የጋራ ቋንቋን መማር እንደሚያስፈልጋቸው ያስገነዝበናል። ስለዚህም አማርኛ በአገሪቱ ውስጥ የሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦች በአገር ውስጥ ሊያግባባ

የሚችል ቋንቋ እንደሆነና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ለጋራ መግባቢያነት የተመረጠ ቋንቋ በመሆኑ በአገሪቱ እንደ አንድ የትምርት አይነት በትምህርትነት መሰጠት እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡

በተጨማሪም ፖሊሲው ህፃኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲማር መብት ቢሰጠውም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አማርኛ ቋንቋን እንዲማር የሚያደርግ ነው፡፡ አማርኛ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተወካዮቹ አማካኝነት የወሰነና በህገ መንግስታቸው ውስጥም እንዲሰፍር ያደረገ በመሆኑ ተማሪው አማርኛ ቋንቋን የመማር ግዴታ እዲኖርበት ማድረግ ትክክለኛ ነው (1994፤65) ፡፡ ይህም ቋንቋውን እንዲማሩት ፖሊሲው የሚያስገድድ መሆኑን በአጽንኦት ያስረዳል፡፡ ከላይ በተሰጠው ሀሳብ መሰረት በአሁኑ ጊዜ በየክልሉ ያሉት የትምህርት ባለሙያዎች በስርዓተ ትምህርት ውስጥ አማርኛን እንደ አንድ ትምህርት በመውሰድ በተገቢው መንገድ እንዲማሩት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በኦሮሚያ ክልልም ትምህርቱ ከአምስተኛ ክፍል ቢጀምርም በትምህርትነት በመሰጠት ላይ ነው ያለው፡፡

## 2.2 ሥነ ትምህርታዊ ስነልቦና (Educational Psychology)

ሥነ ትምህርታዊ ስነ ልቦና (educational psychology) የሰውን መሰረታዊ ባህሪ የሚያጠና የጥናት መስክ ሲሆን ስነ ትምህርት እንዴት ተግባራዊ መሆን እንደሚችል እና ሥነልቦና በትምህርት ተግባር ላይ የሚውልበትን መንገድ ያጠናል፡፡ በተጨማሪም ሥነ ትምህረትዊ ስነ ልቦና በእውቀት መስክ ዙሪያ ህግና መመሪያን በማውጣት እንዴት ተግባር ላይ እንደሚውል ያጠናል፡፡ እንዲሁም እውቀት ከማህበራዊ ሂደት የሚመጣ መሆኑን፣ የእውቀት መሳሪያዎችን፤ዘዴዎችን፤ የጥናትና የምርመር መንገዶችን የሚያጠናና የሚያሳይ መስክ ነው፡፡

Skinner (1989) የሥነ ትምህርታዊ ስነልቦናን የጥናትን አድማስ ሲገልፁ የተስተምህሮት ጥበበን፣ በተስተምህሮት ላይ ችግር የሚፈጥሩ ጉዳዮችን፤ ግለሰባዊ ልዩነቶቸችን፣ የመማር ማስተማር ሂደት ምቹ መንገድ፣ መምህር በማህበረሰብ ውስጥ የሚኖረውን እንቅስቃሴ፣ በጋራ በመማር ሂደት የሚመጣ ውጤት፤ ልዩ ልዩ የማስተማር ዘዴዎችን ወዘተ አካቶ በመያዝ የሚያጠና የጥናት መስክ ነው ይላሉ፡፡

በተጨማሪም ስለ ሰዎች ሰብእና (Personality) በተመለከተ የልጆችን፣ የአዋቂዎችና ተማሪዎችን፣ በትምርት ቤት ውስጥ እና ውጭ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ ለመማር ማስተማሩ ሂደት መፋጠን ሲባል ልዩ ልዩ ጥናቶችን ያጠናል፤ ይመረምራል፤ ለችግሮችም መፍትሔ ያፈላልጋል፡፡ በተጨማሪም ስለ ተፈጥሮአዊ፣ አካላዊና አእምሮአዊ እድገት፣ ማህበራዊ እድገት እና ለውጥ፤ የአመለካከት፣ የፍላጎትና የንሺ ሁኔታዎችን

አእምሮአዊ የመማር ችሎታን፣ የክሂል ትምህርቶችን የመማር ሂደትን፣ የተለያዩ አደ-ጥበቦችን አስመልክቶ እንዴት ተግባር ላይ እንደሚውሉና የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከነመፍትሄአቸው አጠቃሎ የሚይዝ የጥናት መስክ ነው፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ተማሪዎች ትምህርቱ ላይ ያላቸውን አሉታዊና አዎንታዊ ጎኖችን በማጥናት የመማር ማስተማሩ ሂደት የተቃና እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የስብእና መግለጫ የሆኑት እንደ አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ ስሜት፣ ንሺ ወዘተ.. ያሉት በአካባቢአዊ ማህበራዊም ሆነ በትምህርት ላይ የሚያደርሱትን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅእኖዎችን በሙሉ በመዳሰስ፣ በመለየትና ጥናት በማከናወን ችግሮችን የሚፈታ የጥናት መስክ ነው፡፡

በአጠቃላይ ስነ-ትምህርታዊ ስነልቦና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን ለይቶ የሚያሳይና የሰው ልጅ በስነ ትምህርት ዙሪያ ያለውን አጠቃላይ ገፅታን በማሳየት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር የጥናት መስክ ነው፡፡

## 2.3 ፍላጎት ምንድን ነው?

ስለፍላጎት ምንነት የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ የሁሉም ሃሳብ ወደ አንድ ጉራ ሊካተት የሚችል ነው፡፡ (Noll (1979); Craig (1979); buglsk (1971); እና Skinner 1985) ፍላቶት የስብዕና መገለጫ አንድ አካል ሲሆን እንደ ንሺና አመለካከት ሁሉ በስነልቦና ጥናት መስክ ከሚተኮርባቸው ተላውጦዎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Hamlin (1996) ፍላጎትን ሲገልጽ አንድ ድምፅ እንደተሰማ ማዳመጥ ይጀምራል፡፡ ከዛም ስለ ጉዳዩ በማስተዋልና የልብ ትርታ በፍጥነት እየመታ ማሰብ ይመጣል፡፡ በመጨረሻም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ከልብ ማዳመጥና የሚደመጠውንም በማስተዋል ሙሉ በሙሉ በስሜት በመዋጥ ስለ ጉዳዩ እናስባለን፡፡ ይህ የማሰብ ስሜት ፍላጎት ይባላል በማለት ይገልፃሉ፡፡

Craing (1979) እና Turne (1997:136) ፍላጎት ማለት አንድ ግለሰብ ስሜቱንና ዝንባሌውን የሚገልፅበት መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም የአንድን ነገር ምንነት ለማወቅ ትኩረት ሰጥቶ እንዲመለከት የሚገፋፋ ሐይል ነው፡፡ ይህም አንድን ነገር እንድንወደው ወይም እንድንጠላው የሚያደርግ ንቃተ ህሊናዊ ስሜት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

Harlock (1972) ፍላጎትን አስመልክተው ሲገልፁ ፍላጎት ማለት የስብእና የሆነና ወደ ተወሰነ ግብና አላማ፣ እንዲሁም ወደ ተግባር ሊመራን የሚችል ነው፤ ስለ አንድ ነገር የመውደድና የመጥላት ሃይል ነው፤ በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከላይ በቀረበው ገለፃ መሰረት ፍላጎት በአንድ በተወሰነ ነገር ላይ ያተኮረና ወደ ተግባር፣ እንቅስቃሴና ግብ የሚመራ እንደ የስብእና አካል ነው:: ስለሆነም አንድን ጥሩ ነገር እና ተግባር ለማከናወን ፈቃደኛ የመሆንና ያለመሆን ምላሽ የሚሰጥበት ውስጣዊ ስሜት ነው ማለት ይቻላል::

Wilson (1971) Wat (1967) ን ጠቅሶ እንደገለፀው ፍላጎት አንድን ነገር ለማከናወን እና ለመተግበር ትኩረት የሚሰጥበት፤ እንዲሁም አንድን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ውስጣዊ ግፊት፤ ዝንባሌ እና ስሜት ነው:: አንድ ሰው አንድን ነገር ለማከናወን ትኩረት ሰጥቶና እራሱን እያዘጋጀ እያለ እንዳያከናውን በሚታቀብበት ጊዜ የንዴትና የብስጭት ስሜትን ሊፈጥር የሚችል ሃይል ነው በማለት ይገልፃሉ::

በሌላ በኩል Skinner (1985) William James (1890) ን ጠቅሶ፤ ፍላጎት የታቀደን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከናወንን ተግባር መውደድ እና አለመውደዳችንን የሚያመለክት ውስጣዊ ኀሺ እና ለተፈለገ ነገር ትኩረት እንዲሰጥ የሚያደርግ ግፊት፤ ዝንባሌ እና ስሜት ነው በማለት ይገልፃሉ:: እንዲሁም Skinner (1985) Baridie (1946) ጠቅሰው ፤ ፍላጎት ማለት በአንድ ነገር ለመሳብ (ለመማረክ) ወይም ለመገፋት ምክንያት የሚሆን ውስጣዊ ተግባር ነው፤ በማለት ይገልፃሉ:: ባጠቃላይ ብዙ ጥናቶች እንደሚገልፁት ፍላጎት ማለት ከመውደድና ከመጥላት ጋር በተያያዘ መልኩ አንድን ነገር ለመምረጥ ወይም ላለመምረጥ ምክንያት ሊሆን የሚችል የሥብዕና ክፍል ነው:: ይህም አንድን ሁኔታ በመለማመድና ስለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ወደ ተግባር ለመለወጥ ሲባል የሚመጣ ስሜት ነው:: ስለዚህ ፍላጎት ህያው የሆነ አንድን ነገር ጥቅሙን እና አሰራሩን ለማወቅ የሚገፋፋ ሃይል ነው በማለት ሰፊ ማብራሪያ ያቀርባሉ::

ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች እንደምረዳው ፍላጎት ማለት አንድን ተግባር፤ ጉዳይን ለማከናወን የሚያደረግ ተነሳሽነትን፤ መውደድና መጥላትን የሚያመለክት የስብዕና አካል መሆኑን የስገነዝባሉ::

ፍላጎትን ከተለያዩ ተግባራት አንፃር ስንመለከት ደግሞ የሰው ልጅ የተለያዩ ፍላጎቶች አሉት:: እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ የትምህርት ፍላጎት:- አንድ ተማሪ ትምህርቱን ለመማር ያለው ውስጣዊ ስሜት ያመለክታል:: Skinner (1985):: Hamilin (1996) የትምህርት ፍላጎትን ሲገልፁ የትምህርት አይነትን ለማወቅና ለመማር የመፈለግ ሁኔታ ነው ይሉታል:: ይህም ሁኔታ የትምህርት አይነትን ለማወቅ መፈለግ ነው:: ትምህርቱ ስለምንድነው የቀረበው፤ ምንን ለማከናወን

ይረዳል? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስና የሚከናወን ተግባርን መውደድ እና አለመውደድን የሚያመለክት ተግባር ነው።

ለ) የሥራ ፍላጎት:- አንድ ሰው አንድን ስራ ለመስራት ያለው የስራ ምርጫ ነው። የስራ ምርጫም ከግለሰብ ግለሰብ ይለያያል። ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝ ስራን ይመርጣል። አንዳንዱ ደግሞ ሰው ያስከብራል በሚል ሳቢያ አንድን የስራ አይነት ይመርጣል እናም የምርጫ መስፈርታቸው የተለያየ ነው። በመስፈርታቸው መሰረትም የሚመርጡት የስራ አይነት አንዳንዱ መምህርነት፣ ሀኪምነት፣ ነጋዴነት፣ ደላላነትን እና የመሳሰሉትን ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ሰዎች ስራቸውን ሲመርጡ ካላቸው ውስጣዊ ፍላጎት አንፃር መሆኑን እንገነዘባለን።

ሐ) ግለሰባዊ ፍላጎት (Personal Interest):- የአንድን ግለሰብ የተወሰነ ነገርን ወይም ጉዳይን መምረጥ እና ማከናወን የሚያመለክት ሲሆን ግለሰቡ የሚያከናውነውን ተግባር መስራትን የሚያስወደድና አንድን ስራ ሁኔታ መምረጥን ያጠቃልላል (Skinner 1985)።

## 2.4 ፍላጎትና የሁለተኛ የቋንቋ ትምህርት

Machky (1965) እና Schonell (1961) ፍላጎት በቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን ሚና ሲገልጹ የትምህርቱ ይዘት ምን ያህል ከተማሪዎች ተነሳሽነት ና ፍላጎት ጋር ይጣጣማል /አብሮ ይሄዳል? የሚለውን ለመወሰን ይጠቅማል ይላሉ። ምክንያቱም ተማሪው ቋንቋውን ለመማር ፍላጎት ከሌላቸው የተዋጣለት የሚባል ዘዴ እንኳን ቢኖር ኮርሱን ለማስተማር ምንም ላይፈይድ ይችላል። ተማሪው ቋንቋውን ለምን እንደሚፈልገው ወይም የትኛውን ክህሎት ለማዳበር እንደሚፈልግካላወቀ ለትምህርቱና ቋንቋው ስለሚነገርበት ሀገር ለማወቅ ያለው ዕኑ ጉጉት ላይ አሉታዊ ችግር ሊያስከትል ይችላል።

ተማሪው ለትምህርቱ ያለው የፍላጎት ደረጃ በትምህርቱ የተለዩ ክፍሎች ውስጥ ሊለያይ ይችላል ምክንያቱም ንግግርን ለማላመድ የምንገለገልበት ዘዴ ማንበብና መፃፍን ከምናስተምርበት ጋር አንድ ዓይነት አይደለምና። በመሆኑም የተማሪዎችን የፍላጎት ሁኔታ ለየይቶ መገምገም የግድ ያስፈልጋል። ይህንንም በተናጠል ስንመለከት የሚከተለውን ይመስላል።

### 1. ማዳመጥና መናገር

በትምህርቱ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ሁነቶች (አውዶች) ተማሪው በእውነትም ይከሰታል ብሎ የሚያምናቸዉ ናቸዉ? ሁነቶቹን ተማሪው ከዚህ ቀደም

ከሚያውቀውና ሊጠቀመው ከሚችል ነገር - - ከቤቱ፣ ከቤተሰቡ፣ ከሥራው፣ከ- - ጋር አያይዞ ሊገልፃቸዉ ይችላል? ተማሪው ቋንቋውን ከሚማርበት ዓላማ ጋር ይዛመዳሉ? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በሙሉ ለመመለስ ይረዳል።

## 2. ማንበብና መፃፍ

ለንባብ የሚቀርቡ ፅሑፎች የተማሪውን ፍላጎት ይጠብቃሉ/ ይመጥናሉ? ለተማሪው የስሜት እርከን ይቀርባሉን? ንባቡ የተማሪውን ስሜት ይበልጥ የመሳሰሉትን ጥያቄዎችን የሚያነሳሳ ከሆነ የተማሪውን ስሜት የመያዝ (የመግዛት) አቅም ከፍተኛ (ጥልቅ) ይሆናል፤ ለረጅም ጊዜም አያረሳውም፤ እንዲሁም ታሪኩንም ሆነ ታሪኩ የቀረበበትን ቋንቋ በቀላሉ (በፍጥነት) ያስታውሰዋል። ምክንያቱም በፅሑፍ ውስጥ የልብ ሰቀላ ሊኖር ይችላልና፣ ለምሳሌ እንደ ግጭት፣ ቶክከር (የገፀባህሪያት) ና በአንድ አስጨናቂ ታሪኮች ውስጥ የሚገኝ ዓይነት አንጥልጥል ታሪኮች። ይሁን እንጂ ሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ የንባብ ዝንባሌ ላይኖራቸው ይችላል ወይም ማንበብ የሚፈልጉት ነገር የተለየ ነው። ለምሳሌ ያህል ወጣት ወንዶች ከልጃገረዶች የበለጠ አስጨናቂና የጀግንነት ታሪኮችን ማንበብ ይፈልጋሉ። ሌሎች ተማሪዎችም ደግሞ ምናልባት እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተና መረጃ የሚሰጥን ፅሑፍ ማንበብ ይመርጡ ይሆናል። ስለዚህ ትምህርቱ የተማሪዎችን የፍላጎት ሰብጥር ሊያሟላ (ሊያመጣጥን) የሚችል ምንባቦችን ይዟል እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የተማሪዎቹን ፍላጎት ማጤን ወሳኝ ጉዳይ ነው።

Harmer (1991) እንደ'ን ቋንቋ ለመማር የምንነሳው አላማን መሰረት አድርገን ነው። አላማ ደግሞ ለቋንቋው ትምህርት ፍላጎት እንዲኖረን ያደርጋል። በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ፍላጎት እንዲኖር ምክንያታዊ የሆነ አላማ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ቋንቋ ከእለት ተእለት ተግባራችን ጋር የቀረበ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ቋንቋው በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ሁሉ ጠቃሚ ሆኖ የሚገኝ ከሆነ ቋንቋውን ለመማር በከፍተኛ ደረጃ ፍላጎት ያሳድራል።

በሌላ በኩል ለአንድ ቋንቋ ትኩረት ሰጥተን የምንናገረው፣ የምናዳምጠውና የምናጠናው፣ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። አንደኛው ከፍላጎት አንፃር ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንፃር ነው። በመሆኑም አንድ'ን ፅሑፍ የምናነበው ወይም ንግግርን ከልብ የምናዳምጠው ለማንበብና ለማዳመጥ ፍላጎት ሲኖረን ነው።

ለምሳሌ አንድ መፅሔት የሚያነብ ሰው ከመፅሔቱ ውስጥ በቅድሚያ የሚመርጠው ርዕስ ጉዳይ ከፍላጎቱ ጋር ግንኙነት ያለውን ነው። አንዳንድ ጊዜ ትንሽ ገጽ ካለው ርዕስ ጉዳይ ይልቅ፣ ብዙ ገፅ ያለውን ርዕስ ጉዳይ የምንመርጥበት ጊዜም አለ። መፅሐፍ አንባቢው ከቤተ መፃሕፍት

ውስጥ የሚወደውን እና የሚፈልገውን መፅሐፍ መርጦ ያነባል። ምክንያቱም የሚወደውን ርዕስ ጉዳይ መምረጥ እንዳለበት አእምሮው ስለሚያስገድደው ነው።

በተመሳሳይ አንድ ሬድዮ አድማጭም ለራሱ አስደሳችና አነቃቂ ነው ብሎ ያመነበትን መርጦ ያዳምጣል። ከዚህም እንደምንረዳው የምናዳምጠው ወይም የምንሰማውና የምናነበው ከፍላጎታችን አንፃር ነው። ወይም ከሚሰጠን ደስታና ተዝናኖት አንፃር ሊሆን ይችላል። ስለዚህም አንድን ቋንቋ ለመማር ፍላጎት ሊኖረን ይገባል የሚባለው በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ አንድን ነገር በራስ ተነሳሽነት ማንበብ፣ማዳመጥ፣ መማርና መፃፍ እንዲቻል ነው። የሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር ተማሪው በቋንቋው ላይ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲኖረው ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። በዚህ ሁኔታ የሚከናወን የቋንቋ ትምህርት ከተማሪው ውስጣዊ ንሺ ስለሚኖር የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ ይሆናል በማለት ሊቃውንቱ ይገልጻሉ።

### 2.4.1 የፍላጎት ጠቀሜታ

የተለያየ ምሁራን እንደሚገልፁት አንድ አላማ ጥንካሬ እንዲኖረውና፣ ግቡን እንዲመታ ፍላጎት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። አንድን ተግባር የሚያከናውን አካል ለተግባሩ የፀና ፍላጎት ካለው ስራውን በወቅቱ እንዲያከናውን ግፊት ያደርግበታል። አላማን መሰረት አድርጎ የሚከናወን ተግባር ከፍላጎት ጋር ተያያዥነት ያለው መሆን አለበት ምክንያቱም ሙሉ ሃይልን ለመጠቀምና ተግባርን ለማከናወን ይረዳል (Schonell: 1970; Garry 1970) ::

Harmer (1991) እና Buglesk (1971) ሰዎች ለአንድ ተግባር ወይም ጉዳይ ፍላጎት የሚኖራቸው ከሆነ ተግባሩን ለማከናወን ሰፊና ውስጣዊ የሆነ ተነሳሽነትና ግፊት እዲኖራቸው ያደርጋል። Schonell (1970) አንድ አንባቢ ለሚያነበው ምንባብ ከፍተኛ ፍላጎት ካለው በደንብ ስለሚያነበው የማንበቡ ሂደት ግብ መቺ ሊሆን ይችላል። ለማንኛውም ለሚከናወን ተግባር ፈቃደኛና ደስተኛ ያደርጋል።

### 2.4.2 ፍላጎት በትምህርት ውስጥ ያለው ሚና

ሊቃውንት ስለ ፍላጎትና ትምህርት አስመልክተው ያላቸው አመለካከት የተለያየ ነው። Buglsk (1971) ተማሪው ለትምህርቱ አዎንታዊ የሆነ ፍላጎት ሊኖረው ይገባል። ለመማር ፍላጎት የሌለው ከሆነ ትምህርቱን ፈፅሞ ሊማር አይችልም። ስለዚህ አንድን የትምህርት አይነት ለማስተማር በምንነሳበት ጊዜ ተማሪው ለሚማረው ትምህርት የሚኖረው ፍላጎት አስቀድሞ ሊታወቅ ይገባል። ፍላጎት ካለው ትምህርቱን በተገቢው መንገድ መከታተል (መማር) ይችላል።

ፍላጎት የሌለው ተማሪ ግን ትምህርቱን በተገቢው መንገድ መከታተል አይችልም፡፡ የመማር ፍላጎት የሌለውን ተማሪ ማስተማር አስቸጋሪ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

ፍላጎት የሌለውን ተማሪ እንዴት መለየት ይቻላል የሚለውን Skinner (1959) ሲያብራሩ፤ ተማሪው የሚሰጠውን ትምህርት ከልብ የማይከታተል ከሆነ፣ ትምህርቱ ሲሰጥ ከልብ የማያዳምጥና በትክክል መረዳት የማይችል ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪው የመማር ፍላጎት የሌለው መሆኑን ያመለክታል ይላሉ፡፡ ተማሪው በሚሰጠው ትምህርት ምንም ፍላጎት የሌለው ከሆነ ደግሞ የመማር ማስተማሩ ተግባር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተማሪው ለሚሰጠው ትምህርት ፍላጎት እንዲኖረው የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ተማሪው በትምህርቱ ፍላጎት እንዲኖረው መምህሩንም ሆነ ማህበረሰቡ ተማሪዎችን ለትምህርታቸው መቀስቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አለበለዚያ ግን ለትምህርቱ ፍላጎት የሌለውን ተማሪ ማስተማሩ በክፍል ውስጥ ለሌላ ተማሪ እንደ ማስተማር ይቆጠራል፡፡ በአጠቃላይ ተማሪው የመማር ፍላጎት (learning interest) ከሌለው የሚሰጠውን ትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ለመከታተል አይነሳሳም፡፡ ንሺ (motivation) ደግሞ ከፍላጎት የሚመጣና ጥብቅ ተያያዥነትም ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

እንደ Schonell (1986) አገላለፅ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲማሩና ጉጉት (Curiosity) እንዲያድርባቸው ፤ በቅድሚያ ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ የሆነ ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የተማሪዎች ፍላጎት ከሚማሩት አርዕስት ጉዳይ ጋር የሚገናኝ ከሆነ ደግሞ ቀደም ብሎ ካላቸው እውቀት ጋር አያይዘውና አዋህደው እንዲገነዘቡትና በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ካላቸው እየተሰጠ ያለውን ትምህርት በቀላሉ ሊረዱትና ሊያውቁት ከመቻላቸውም በላይ፤ የተማሩትን ለረጅም ጊዜ በአዕምሯቸው ይዘው እንዲቆዩ፤ በተማሩትና በሚያነቡት ሁሉ እንዲደሰቱ፤ ጥሩ ልምድና ተግባር እንዲኖራቸው፤ ውስጣዊ ንሺ ወይም ውሁዳዊ ንሺ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ፍላጎት በትምህርቱ ሂደት ለሚከናወን ማንኛውም ተግባር ግብ መምታት የራሱን አስተዋፆኦ ያደርጋል፡፡ ስለዚህም የሚሰጠው የትምህርት አይነት ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ተያያዥነት ሊኖረው የግድ ነው፡፡

Skinner (1989) ና Schon'ell (1961) ተማሪዎች እንደየ እድሜአቸው ፍላጎታቸውም ሆነ ተግባራቸው ይለያያል ይላሉ፡፡ በዚህም መሰረት እድሜአቸውን መሰረት ያደረገ ትምህርት ከተግባርና ፍላጎታቸው ጋር ተቀናጅቶ የሚሰጥ ከሆነ የመማር ማስተማሩ ሂደት በአግባቡ ሊከናወን ይችላል፡፡ ሂደቱም ግብ መቺ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል የአምስት አመትና የአስር ዓመት ተማሪ ያላቸው ፍላጎት የተለያየ ነው፡፡

ስለዚህም የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችንና ክንውኖች ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር በማቀናጀት የሚተገበሩ ከሆነ ተማሪዎቹ በሚሰጠው ትምህርት ላይ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። በዚህ ሁኔታ የሚከናወን የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ ይሆናል። የመማር ሂደት ስኬታማ የሚሆነው ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፣ በአስተውሎት መመርመርና ፍላጎት ሲኖር ነው። ለትምህርቱ ጥሩ አመለካከት ያለው ተማሪ ደግሞ ጥሩ ፍላጎት እንዲኖረው ያደርገዋል። የነዚህ ነገሮች አዎንታዊ ትንጅት ደግሞ የመመማር ማስተማሩን ሂደት አስደሳችና ግብ መች ያደርገዋል።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው የምሁራኑ ሃሳብ ለመረዳት የሚቻለው ፍላጎት ለትምህርት ከፍተኛ ሚና እንዳለው ነው። ተማሪው ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተልና በአግባቡ እንዲያከናውን ፍላጎት አንዱና መሰረታዊው ጉዳይ ነው። በመሆኑም ያለፍላጎት የመማር ማስተማሩን ሂደት በተገቢው መንገድ ማካሄድም ሆነ በስርአተ ትምህርቱ ላይ  ከተቀመጠው ግብ መድረስ የማይቻል ነው። ስለዚህ በሥርዓተ ትምህርትም ሆነ በመማርያ መጽሐፍ ዝግጅት ሂደት የተማሪዎቹ ፍላጎትም ትኩረት ተሰጥቶት ሊታሰብበት ይገባል።

## 2.4.3 ፍላጎትን ማጥናት ለምን ያስፈልጋል?

Harmer (1991) መምህራን የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት አውቀው ትምህርቱን ከመጀመራቸው በፊት የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት ስለሚረዳ የተማሪዎን ፍላጎት ማጥናት ያስፈልጋል ይላሉ። ምክንያቱም ፍላጎት የንሺ ዋና አካል ስለሆነ የተማሪዎችን ፍላጎት በማንሳሳት ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ንሺ እንዲኖራቸው ለማድረግ ስለሚረዳ ነው። Skinner (1989) እና Craig (1975) እንደሚሉትም ተማሪዎች ለሚቀርብላቸው ትምህርት የየራሳቸው የሆነ ፍላጎት ስላላቸው፣ መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቅ ይጠበቅበታል። ትምህርቱም መቅረብ ያለበት የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት አድርጎ ሊሆን ይገባል። ፍላጎትን መሰረት ካላደረገ ደግሞ ግቡን ላይመታ ይችላል። ይህንንም Harcock (2001) ፍላጎት ያለው ተማሪ ያለ ምንም ንሺ ጥሩ ውጤትን ሊያስመዘግብ ይችላል በማለት ያጠናክራሉ። በአጠቃላይ የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቅ የማስተማር ዘዴን ለመወሰን፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማንሳሳት እና የተማሪዎች ማንነትን ለማወቅ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው።

እንደ Callahan (1988)፣ Buglski (1971) እና Garry (1970) ገለፃ ደግሞ፣ በክፍል ውስጥ የሚከናወነን ተግባር በብቃት ለማካሄድ፣ ከተማሪው ችሎታ፣ ተሰጥኦ፣ ዝንባሌ እና ግብ ጋር አብሮ የሚሄድን የትምህርት ዕቅድ ለማዘጋጀት ፍላጎትን ማጥናት አስፈላጊ ነው።

ስለዚህ መምህሩም የመማር ማስተማሩን መቶት በትክክለኛው ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር መሄድ በሚችል መንገድ ማደራጀት አለበት፡፡ ለዚህም በተቻለ መጠን የተማሪዎችን ስብእና፣ ባህሪ እና የችሎታ ደረጃ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ይህንንም መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ተቀራርቦ በመስራትና በአንዳንድ ጉዳዮች ላይም በመወያየት ማወቅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በቃለምልልስ፣ በውይይት፣ በምልከታ የተማሪዎችን ባህሪ እና ፍላጎት ማጥናትና ማወቅ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ክንውኖችና መልመጃዎችን (ልምምዶችን) ተማሪዎቹ ሊወዷቸው ከሚችሉ ተግባራት ጋር አብሮ ለማዛመድ የሚረዱ የተለያዩ ስልቶችን ለመወሰን የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናቱ አስፈላጊ ነው፡፡

Skinner (1959) የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናት ስለ ተማሪው ማንነት ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ ተማሪዉ ለትምህርቱ ያለው ፍላጎት አዎንታዊ ከሆነ ይህንኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ ጠብቆ ለማቆየት የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቁ ወሳኝ ነው፤ ይላል የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ ማወቁም ለሚቀርበው ትምህርት እንደ መሸጋገሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

በአጠቃላይ በተለያዩ የስነልቦና ሊቃውንት አገላለፅ ማንኛውም ሰው እራሱን ለትምህርት ካላዘጋጀ በቀር ትምህርቱን በትክክል መማር አይችልም፡፡ ስለዚህም በርካታ የስነ ልቦና ሰዎች ተማሪዎች በትምህርታቸው የሚማሩበትን መንገድ ለማወቅና እንዲሁም ለማጠናከር ብዙ ጥናቶችን ያከናወናሉ፡፡ ምክንያቱም ያለፍላጎት በአጋጣሚ የሚከናወን ትምህርት ግቡን አይመታም፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት እና ጉጉት እንዲያድርባቸው ለማድረግ፣ አስፈላጊና ተገቢ የሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለመጠቀም ተማሪዎቹ በትምህርቱ ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው ወዘተ... ለማድረግ የተማሪዎቹን ፍላጎት ማጥናቱ አስፈላጊ ነው ይላሉ፡፡

በHarmer (1981) አገላለፅም የተማሪዎችን ዳራ ማወቅ ተገቢ የሆነውን የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመጠቀምና፣ ከተለያዩ የተማሪዎች ህይወት ገጠመኝ ጋር እያይዞ ለማቅረብ ይጠቅማል፡፡ ከቋንቋ ትምህርት አንፃርም ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋን ለምን መማር እንደሚፈልጉና ቋንቋውንም ምን ያህል እንደሚወዱት ለማወቅ የተማሪዎችን የህይወት ዳራ ማወቅ አስፈላጊ ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

ስለዚህም የተማሪዎችን ማንነት ለማወቅ የተማሪዎችን ታሪክ የሚገልፁ ጥያቄዎችን በማውጣት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎችን ታሪክ የሚገልፁ ጥያቄዎችም፣

ሀ/ እድሜ ለ/ ጾታ ሐ/ ማህበራዊና ባህላዊ ዳራ መ/ የሥራ ሁኔታ ሠ/ ንስሺ/ አመለካከት (motivation/ Attitude) ረ/ የትምህርት ዳራ ቀ/ እውቀት በ/ ፍላጎትና እምነት

(Interest and Blive) ምንነትን በመጠየቅ በሚቀርበው ምላሽ መሠረት ምን አይነት የማስተማሪያ መሳሪያ መምረጥ እንደሚያስፈልግ ለመወሰን ይረዳል፡፡ በዚህ መንገድ የተማሪዎችን ታሪክ ማወቅ ምን አይነት መሳሪያዎች ለተማሪዎቹ ትክክለኛ እንደሚሆን ለማወቅና ለመረዳት ይረዳል፡፡

ከዚህ ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው የተማሪውን ማንነት እና ፍላጎትን ማወቅ የሚያስፈልገው ለተማሪው ምቹ የሆነ ትምህርት ለመስጠትና የተለያዩ መሳሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም እንዲቻል ለመርዳት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ የሁሉንም ሊቃውንት ገለፃ መሰረት በማድረግ ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው ተማሪዎች ለትምህርታቸው ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ በተማሪዎች ዙሪያ ጥናት ማካናወን ያስፈልጋል፡፡ ጥናቱ የሚያስፈልግበት አብይ ጉዳይ የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችን ለመጠቀም፣ የትምህርት እቅዶች ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር ለማቅረብ፣ እንደየ ጾታቸዉ ና እድሜያቸዉ ትምህርቱን ከፍላጎታቸዉ ጋር አጣጥሞ ለማቅረብ በእድሜና በፆታ መሃከል ያለውን የፍላጎት ልዩነት ማወቁ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ስለዚህ ለተለያዩ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ የተማሪዎችን ፍላጎትና ማንነት ማጥናት አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆን ነው የምሁራኑ ገለፃ የሚያስረዳው፡፡

### 2.4.4 የተማሪዎችን ፍላጎት የማወቅያ ዘዴዎችና መንገዶች

እንደ Callahan (1988) እና Bugelski (1971) የተማሪዎችን ማንነትና ፍላጎትን ለማወቅ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ዘዴዎችም፤

1. በማህደራቸው ላይ የቀረበውን ሪኮርድ ማየት፡- ከትምህርት ቤቱ ቢሮ፣ ከምክር አገልግሎትና ከትምህርት ክፍሉ የተማሪውን ማህደር በመጠየቅና በማየት የተማሪዎችን ማንነት ማወቅ ይቻላል፡፡ እንዲሁም መምህሩ በየጊዜው ስለተማሪው የመዘገበውን ታሪክ ከአስተዳደር፤ ከምክር አገልግሎት ሰጭው (guidance personal) የተለያዩ መረጃዎችን በመውሰድ ስለተማሪው ትምህርታዊ ዳራ (Acadamic background) እና ማንነት ማወቅ ይቻላል፡፡ እንዲሁም ማዕከላዊነቱን የጠበቀ ፈተና (Standerdized test) አዘጋጅቶ በመፈተንና ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን በማየት የተማሪውን ማንነትና ፍላጎት ማወቅ ይቻላል፡፡

2. ምልከታ (Observation) :- ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን ተግባራት በሚዳሲጫወቱ፣ እና በተለያዩ ቦታዎች የሚያከናወኑትን በማየት የተማሪዎችን ሰብእናና የአቅም ደረጃቸውን ማወቅ ይቻላል።

3. በስብሰባ (Conference):- ከተማሪዎች ጋር የስብሰባ ውይይት በማከናወን የተማሪዎችን ፍላጎት ምኞት (Ambitions)፣ ችግር አለኝታ፣ ተስፋ (Hopes) እና ሌሎች ነገሮችን በማወቅ የሚሰጠውን ትምህርት ከነሱ ሰብእና፣ ችሎታ እና ፍላጎት ጋር በሚሄድ መልኩ ለማዘጋጀት ተማሪውን ማወቅ ያስፈልጋል። በስብሰባ መልክ መረጃ በምንሰበስብበት ጊዜ ማከናወን የሚያስፈልግ ተግባር

   ሀ. ክፍት የሆነ ጥያቄ ብቻ በመጠየቅ (Ask open- ended questions) ተማሪዎች በነፃነት ውይይት እንዲያደርጉ በመፍቀድና በማበረታታት ምን እንደተናገሩ መመዝገብ ነው።

   ለ. ሞራላቸውን መጠበቅ:- ተማሪዎች ሃሳባቸውን በሚያቀርቡበት ስአት ባለመከልከል ምን ሃሳብ እና መልዕክት እንዳቀረቡ በመቀበል ያቀረቡትን ሃሳብ በአግባቡ በመመዝገብ ሞራላቸውን ማወቅ እና

   ሐ. ከስብሰባው በኋላ አጠቃላይ የቀረበውን ሃሳብ በአግባቡ መመዝገብ ናቸው

4. የቤተሰብ ስብሰባ ማካሄድ (Parent conferences)፣ የቤተሰብ ስብሰባ በማድረግ ስለተማሪዎቹ ብዙ መረጃን መሰብሰብ ይቻላል። ቤተሰቦችም ስለ ልጆቻቸው ብዙ መረጃዎችን ይሰጣሉ። ስለዚህ ለቤተሰብ ጥያቄ በማቅረብ የሚመለሰውን መልስ በአግባቡ በመመዝገብ መረጃ መሰባሰብ ይቻላል።

5. የራስ የህይወት ታሪክ (Auto-biographies)፣ የተለያዩ የህይወት ታሪክን የያዙ ደብዳቤዎች (ወረቀቶችን) በማንበብ በሰውየው (በተማሪው) ላይ የቀረቡ መረጃዎችን መመልከት ነዉ። የራስን ታሪክ አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፣

   ሀ/ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትህን በጨረስክበት ጊዜ ምን ለመስራት አቅደህ ወይስ አስበሃል?

   ለ/ ሥራ አለህ? መልስህ አዎን ከሆነ ምን አይነት ሥራ ነው? ስራውን ትወደዋለህ?

   ሐ/ ማንበብ ትወዳለህ? በአብዛኛው የትኛውን ክፍል ትወዳለህ?

   መ/ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ አለህ? የትርፍ ጊዜህን ለማሳለፍ የምትጠቀምበት ዘዴ ምንድ ነው?

6. በመጠይቅ፡- በመጠይቅ የሚቀርቡት ጥያቄዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

ሀ) የፍላጎት ማወቅያ መጠይቆች (Interest finder)፤

ፍላጎትን ለማወቅ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ሲባል ለምሳሌ ያህል የትኛውን የቴሌቭዥን ፕሮግራም በይበልጥ ትወዳለህ? እስፖርት ትወዳለህ? የትኛውን የእስፖርት አይነት ትወዳለህ? እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ብዙውን ጊዜ የአንድን ግለሰብ እና የማህበረሰብ ፍላጎትን ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎችን ዘርዝር አድርገን ስንመለከታቸው የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

1. ከጓደኛህ ጋር ካፍቴሪያ በምትሆንበት ጊዜ አብዛኛውን ስለምን ጉዳይ ታወራላችሁ?
2. ማንበብ ትወዳለህ?
3. ምን አይነት ፅሑፍን በብዛት ታነባለህ?
4. በየቀኑ የሚወጡ ጋዜጦችን ታነባለህ?
5. የምታነብ ከሆነ ብዙውን ጊዜ የትኛውን ክፍል ታነባለህ?
6. የትኛው ፊልም የደስታ ስሜትን ይፈጥርልሃል?
7. ሁል ጊዜ ቴሌቭዥን ትመለከታለህ?
8. አዎን የምትል ከሆነ የትኛውን ፕሮግራም በይበልጥ ትወዳለህ? የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ለ) የራስ ፍላጎትን አስመልክተው የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በተመለከተ በተራ ቁጥር አምስት ስር የቀረቡትን በሙሉ ይመለከታል፡፡ ስለዚህ በተራ ቁጥር አምስት ስር ያሉት በዚህ ስር ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ ካላይ የቀረቡት ዘዴዎች በሙሉ የተማሪዎችን ፍላጎቶና ማንነትን ለማወቅ የሚረዱ ዘዴዎች ሲሆኑ በርዕስ ጉዳዩ መሰረት ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በመጠየቅ የተማሪዎችን ፍላጎት ማንነት ማወቅ ይቻላል፤ በማለት ሊቃውንቱ በዝርዝር ያቀርባሉ፡፡

Skinner (1985) "የፍላጎት መስፈርት (መለኪያ)" በሚለው ርዕስ ውስጥ ፍላጎትን ለማወቅ የምንጠቀምበት ስልትና ዘዴዎች ሲገለፁ ቃለ መጠይቅን በስብሰባ መልክ በማቅረብ፤ ለጓደኞቻቸው ሪፖርት እንዲደርጉ በማድረግ እና የተለያዩ መጠይቆችን በማዘጋጀትና በመጠየቅ በቱ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት ተከታታይ አሰሳ በማድረግና የጠበቀ ክትትል በማከናወን የተማሪዎችን ፍላጎትና ስብእናን ማወቅ ይቻላል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

### 2.4.5 የፍላጎት መመዘኛ (Interest Inventory)

Buross (1978) እና Craing (1979) የስብእና ክፍል እንደሆነና ከግለሰብ ዳራ፣ ገጠመኝ፣ ችሎታ ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ፍላጎትን እንዴት መለካት እንደሚቻልም እንደሚከተለው ገለፃቸውን ያቀርባሉ::

የሰውን ፍላጎት ለመለካት የሚያገለግል ቀመር ከፈተና እና ከስብእና መለኪያ (Personality Inventory) ጋር ተመሳሳይነት አለው:: በትምህርት ቤት የሚገኙ የምክር አገልግሎት ሰጭዎች ወይም የስነልቦና ሊቃውንት የአንድን ሰው የሥራ ወይም የትምህርት አይነት ምርጫን ለማወቅ የሚጠቀሙበት የፍላጎትን ሥዕል ሊያሳይ የሚችልን መመዘኛ ነው:: መመዘኛውም የአንድን ሰው አንድን ጉዳይ መውደድ እና አለመውደድን ወይም መጥላትን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የሚገኙ የተለያዩ የመልስ ውጤቶችን በመመዝገብና በማስላት ከስሌቱ በተገኘው ውጤት መሰረት ፍላጎት ይለካል::

የፍላጎት መመዘኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው በ E. K Strong (1927 እና 1928) ሲሆን ይህም እስከ 1974 ድረስ በስፋት አገልግሏል:: በመቀጠልም Cambell በ1974 ለሴትም ለወንድም የሚሆን በሰባት አርዕስተ ጉዳይ ላይ የቀረበ የፍላጎት መመዘኛ (ወደ 375 ጥያቄዎችን) አዘጋጀ:: ርዕስ ጉዳዮቹም:-

1. ሥራ
2. የትምህርት አላማ
3. ጫወታ ወይም ደስታ
4. ተግባራት
5. የሰው አይነቶች
6. ከሁለት በላይ ተግባራት ውስጥ አንዱን በመምረጥ እንደ ምርጫው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና
7. በአንድ አርዕስተ ጉዳይ ላይ መስማማትን አስመልክቶ የቀረቡ ናቸው (Craig, 1979)::

ከነዚህም ከ1 - 5 ያሉት የአንድን ሰው ግላዊ ምርጫ የሚመለከቱ ጥያቄዎች ናቸው:: በ6ኛው ተራ ቁጥር ላይ የሚገኙት ደግሞ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ አማራጮች ቀርበው በፍላጎት ቅደም ተከተል መሰረት ማስቀመጥን የሚመለከቱ ሲሆኑ በ7ኛ ተራ ቁጥር ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ መስማማት ወይም አለመስማማትን በተመለከተ የቀረቡ

የግል ገለፃዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል አዎን፣ አይደለም ወይም "?" በማለት ለመመለስ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ ናቸው (Callahan, 1988; Craig, 1979)፡፡

የግለ-ራስ መመዘኛ ጥያቄዎች በተለያየ መንገድ ከፍላጎት፣ከአጫጭር የህይወት ታሪኮች ጋር ተቀናጅተው የቀረቡና ከስድስት የተግባር ክፍሎች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል አውናዊ (realistic)፣ ጥናታዊ (Investigative)፣ ጥበባዊ (artistic) ፣ ማህበራዊ (Social)፣ ታታሪነት (enterprising) እና ተለምዶአዊ (Conventional) ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እንዲሁም 23 መሰረታዊ ፍላጎት (እርሻ፣ መካኒክስ፣ ጤና ሳይንስ፣ ማስተማር፣ ንግድ ወዘተ) እና 124 የሥራ መስኮችን (ጥበብ፣ ግብርና፣ ፖሊስ ሃላፊ፣ የስነ ልቦና ሊቅነት፣ መምህር ወዘተ..) በተጨማሪም ከስራ ጋር የተያያዙ የትምህርት ዝንባሌ (Orientation)፣ ከሰው ጋር የማይግባባ (Introvertion) ከሰው ጋር የሚግባባ (extrovertion) በማካተት በሊስት የመቆጣጠሪያ ሰነድ (administrative indexes) ላይ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጥ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ እንዲሁም በSCLL የጥያቄዎች ተገቢነት (validity) እና አስተማማኝነት (reliability) በትክክል የታየ መሆኑም ተገልጿል፡፡ የፈተናው አይነት ብዙ መልክ ቢኖረውም አስተማማኝነቱ በሚዛን (Scales) ላይ 0.80 ይሆናል፡፡ የሥራ ፍላጎትን አስመልክቶ የቀረበው ጥያቄ አስተማማኝነት ደግሞ በ0.60 እና 0.70 መሃከል ላይ እንደሆነ ነው፣ ሊቃውንቱ የሚገልፁት (Craig, 1979)፡፡

### 2.4.6 የሥራ መስኮች ትምህርት አይነት ፍላጎት ቅኝት (Vocational inerest survey)

የትምህርት አይነትን በተመለከተ የሚቀርብ የፍላጎት መመዘኛ ከሌሎች የፍላጎት መመዘኛዎች በመጠኑም ቢሆን ይለያያል፡፡ ይሄም የተማሪዎች ውጤት የሚገለፀው እንደ ፍላጎት ሁሉ በፐርሰንታይል ሲሆን በእያንዳንዱ ውጤት መሃከል ያለውን ልዩነትም ለማወቅ ደግሞ የእያንዳንዱን ውጤት ወደ አማካኝ በመለወጥ በ 'ቲ' ቴስት ቀመር ልዩነቱን ማወቅ ይቻላል፡፡

ሌላው የውጤት መለኪያ መሳሪያ በተማሪዎች የትምህርት ዝንባሌ ላይ ተመርኩዞ ፍላጎትን ሊለኩ የሚችሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለ ትምህርቱ ያለውን የፍላጎት ደረጃ መመርመር ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በሁለተኛ ደረጃ ወይም በኮሌጅ ለሚሰጡ የትምህርት አይነቶች ለምሳሌ እንደ እርሻ፣ ንግድ ዘይ፣ እደ ጥበብ ፣ ማህበራዊ ሳይንስ፣ ባዮሎጂካል ሳይንስ፣ ቋንቋ እና የመሳሰሉትን የትምህርት አይነቶች በተመለከተ ተማሪዎች ያላቸውን የፍላጎት ደረጃ በዚህ የፍላጎት መመዘኛ ማወቅ ይቻላል፡፡ እነዚህ የትምህርት አይነት ፍላጎት የመለኪያ መስፈርቶች በተለያየ መልኩ መቅረብ የሚችሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ባለሶስት 'ስፍርታዊ መለኪያና ባለ አምስት ስፍርታዊ መለኪያዎች የሚጠቀሱ ናቸው (Craing 1979 and Cllahan 1988)፡፡

ባለ ሶስት ስፍርታዊ የሚባሉት ሦስት አማራጮችን የያዙ ሲሆን ባለ አምስት ስፍርታዊ መለኪያ የሚባሉት ደግሞ አምስት አማራጮችን የያዙ ናቸው:: ይሁንና የሰውን ፍላጎት ለመለካት በይበልጥ አመቺ የሚሆነው ባለ አምስቱ ስፍርታዊ መለኪያ እንደሆነ ከድረ ገፅ የተገኘው መረጃ ያመለክታል:: ከባለሶስቱና ከባለ አምስቱ ስፍርታዊ መለኪያዎች ከመለካት አንፃር ሲታዩ ግን ልዩነቱ የጎላ አለመሆኑንም አያይዘው ያስገነዝባሉ (Mitcheil1985; Buros 1959 እና 1979)::

ባለ ሶስተ ስፍርታዊ የፍላጎት መለኪያ የሚባሉትን ሁለት ምሳሌዎችን እንመልከት፤

| | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|
| 1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ትወዳለህ? | እወዳለሁ | አልወሰንኩም | አልወድም |
| 2. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እወዳለሁ:: | እስማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም |

ከላይ የቀረቡት ባለ ሶስት ስፍርታዊ የፍላጎት መለኪያ ሲሆን አዎንታዊ በሆነ መልክ የቀረቡ ናቸው:: አሉታዊ በሆነ መልኩ ሲቀርብ የነጥብ አሰጣጡ በአዎንታዊ በተቃራኒው መንገድ ነው::

ምሳሌ 2. ሁለት ባለ አምስት ስፍርታዊ የፍላጎት መለኪያ

1. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እወዳለሁ::

| 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም | በጣም አልስማማም |

2. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን አልወድም::

| 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም | በጣም አልስማማም |

በምሳሌ ሁለት ላይ የቀረቡት ባለ አምስት ስፍርታዊ የፍላጎት መለኪያ ሲሆን አዎንታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ናቸው:: አማራጫቸውም የቁጥር አሰጣጡ ከአምስት ጀምሮ እስከ አንድ ድረስ ይሆናል:: አሉታዊ ጥያቄ ከሆነ ደግሞ ከ አንድ ጀምሮ እስከ አምስት ድረስ ይሆናል::

ምሳሌ አዎንታዊ

| 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | እስማማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም | በጣም አልስማማም |

ለአሉታዊ ጥያቄዎች

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|
| በጣም እስማማለሁ | እስማማማለሁ | አልወሰንኩም | አልስማማም | በጣም አልስማማም |

### 2.4.7 ፍላጎትና ሥርአተ ትምህርት

መደበኛ ትምህርት፣ ስርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት የሚከናወን ነው። የትምህርቱ ዓላማም ከዚሁ ከስርዓተ ትምህርቱ ላይ ከተቀመጠው አላማ መድረስ ነው። ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችለው ትምህርቱ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ሲጣጣም ነው። ለዚህም በቅድሚያ ስርዓተ ትምህርቱ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ መዘጋጀት አለበት። የተማሪዎቹን ፍላጎት እና ዝንባሌ ከግምት ያስገባ ስርዓተ ትምህርት ደግሞ ግብ መቺ ይሆናል (Bickley 1990; Buglesky 1971; Craing 1979; Skinner 1985)።

Noll and Craing (1979) በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የተማሪን ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ተግባር ዋናና መሰረታዊ ጉዳይ ነው ይላሉ። ምክንያቱም የተማሪዎችን ፍላጎት አስቀድሞ መለካቱና ማወቁ በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት የትምህርቱን አላማ ከተማሪዎች ዝንባሌ፣ አመለካከትና ስሜት ጋር አጣጥሞ ለማቅረብ ያግዛል። በሥርአተ ትምህርት ዝግጅት የተማሪን ፍላጎት ማወቁ የተለያዩ የትምህርት አቅዶችን ለመተግበር፣ ሥርአተ ትምህርትን ወደ ጥሩና ጠቀሚ ደረጃ ለማምጣትና፣ ለማሳደግ፣ የፈተና ፕሮግራሞችን ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አጣጥሞ ለማውጣት፣ የተለያዩ የምርምር ፕሮግራሞችን ለማስተካከልና በአጠቃላይ ምርምር ለማካሄድ ይጠቅማል። ስለዚህም ስርአተ ትምህርትና የተማሪዎች ፍላጎት በአንድ ላይ የሚታሰቡ ጉዳዮች ናቸው (1979፣ 358)።

Skinner (1985) ደግሞ አንድ ስርአተ ትምህርት ሲዘጋጅ የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝንባሌን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት በማለት ይህንኑ ያጠናክራል። ስለዚህም አንድ ስርአተ ትምህርት ከመዘጋጀቱ በፊትም ሆነ ከተዘጋጀ በኋላ የተማሪዎችን ፍላጎት ማወቅና ማጥናቱ አቢይ መሰረታዊና አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ይህንንም ሃሳብ በመደገፍ Craig (1979) የተማሪዎችን

ፍላጎት ማጥናት በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ወቅት ብቻ ሳይሆን በየጊዜው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይም ሆነ በየትምህርቱ ውስጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ ስለ ተማሪዎች ፍላጎት ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ፍላጎት ማጥናት የትምህርት ቤቶች አቢይ ተግባር መሆን አለበት ይላል፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ፍላጎት በተመለከተ ያላቋረጠ ጥናትና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ገለፃዎች እንደምንረዳው፤ አንድ ሥርአተ ትምህርት ሲዘጋጅና ለማዘጋጀት ሲታሰብ የተማሪዎች ፍላጎትም አብሮ መታሰብ እንዳለበትና ሁለቱም የማይነጣጠሉ ተግባራት መሆናቸውን ነው፡፡

## 2.4.8 በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች

በ Tudor (1995) አገላለፅ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የተማሪው ነፃነት፤ የተማሪው ለአንድ ጉዳይ ያለው አመለካከት፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የተማሪው ነፃነት ስንል ተማሪው ከማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ተፅእኖ ነፃ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህም ተማሪው በእራሱ ፍላጎት እየተመራ የሚማር ካልሆነ በትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕና አለው በማለት Tudor (1995). Noll (1979) and Schonell (1965) ይገልፃሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦችም ሆነ በተለያዩ ሊቃውንት በቀረበው ገለፃ መሰረት በተማሪዎች ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ተብለው የሚጠቀሱት 1ኛ) ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት 2ኛ) የማስተማሪያ ዘዴ 3ኛ) ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት 4ኛ) ተማሪው የሚገኝበት ሁኔታ (የተማሪው ገብዝና፤ የሚኖርበት ማህበረሰብ፣ እድሜውና ጾታ ወዘተ) እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህንም ቀጥለን አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን፡፡

### 2.4.8.1 ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከትና ግምት

Cronbach (1963) አመለካት እንደ ማንኛውም የሰብእና ክፍሎች በትምህርት ሂደት ውስጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ለአንድ የትምህርት አይነት ተማሪው ጥሩ አመለካከት ከሌለው ትምህርቱን ለመማር መልካም የሆነ ፍላጎት አይኖረውም፡፡ ተማሪው ለሚማረው ትምህርት ጥሩ የሆነ አመለካከት ካለው ትምህርቱን ለመማር አዎንታዊ የሆነ ፍላጎት ይኖረዋል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ለትምህርቱ አሉታዊ አመለካከት ካለው ትምህርቱን ለመማር አሉታዊ የሆነ ፍላጎት ነው የሚኖረው፤ በማለት ይገልፃሉ፡፡

በሌላ በኩል ከድረ ገፅ በተገኘው መረጃ መሰረት ብዙ ተማሪዎች የሂሳብ ትምህርትን ለመማር አዎንታዊ አመለካከት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁሉም ጥሩ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር አዎንታዊ ፍላጎት እንደሌላቸው ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከድህረ ገፅ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው አሉታዊ አመለካከት ካላቸው ተማሪዎች ይልቅ በአብዛኛውን ጊዜ አዎንታዊ አመለካት ያላቸው ተማሪዎች ናቸው አንድን ትምህርት የመማር ፍላጎት ያላቸው፡፡

በተመሳሳይም Spolsky (1989) ፣Skinner (1985) እና Buglisky (1971) በመለካከት አንድን የትምህርት አይነት በመማር ፍላጎት ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅእኖ ሲገልፁ፤ ተማሪዎች ለአንድ ትምህርት ጥሩ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን ለመማር ጥሩ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ እዲሁም አንድን ትምህርቱም ለመማር ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ደግሞ ለትምህርቱም ጥሩ የሆን አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል በማለት ይገልፃሉ፡፡

ዲንቂሳ (1996) ኢ-አፈፊትና አፈፊት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት አጥንተው፤ የሁለቱም አይነት ተማሪዎች ለቋንቋው ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤት ላይም «አፈፊትም ሆነ ኢ-አፈፊት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የሚጠሉ አይደሉም፡፡» ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ ከዚህም እንደምንረዳው አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ከተማሪዎች የመማር ፍላጎት ጋር አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት እንዳለው እና አመለካከት እና ፍለጎት እርስ በእርሳቸው ተደጋጋፊነት እንዳላቸው ነው፡፡

Hurlock (1972) እንደሚመለከት ደግሞ ተማሪዎች አንድን ትምህርት ምንም ጥቅም አይሰጥም ወይም ትምህርቱ ከባድ ነው የሚል አመለካከት ካላቸው ትምህርቱን የመማር ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡ ፍላጎታቸው ላይ አሉታዊ ተፅእኖን ያሳድራልና፡፡ በተቃራኒው ተማሪዎቹ ትምህርቱ ጠቀሚታ  አለው  ብለው የሚገምቱ ከሆነና ስለትምህርቱ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ካላቸው ትምህርቱንም ለመማር አዎንታዊ ፍላጎት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ ሃሳብም መረዳት እንደሚቻለው፡፡ መገመት የሚቻለው ፍላጎትና አመለካከት አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸው ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው ተማሪዎች ለትምህርታቸው ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ከሆነ ትምህርቱን ለመማር አዎንታዊ ፍላጎት እንዲኖራቸው ተፅእኖ ማሳደር እንደሚችል ነው፤ የተገለፀው መረጃ የሚያመለክተው፡፡

### 2.4.8.2 የመምህሩ የማስተማር ዘዴ (Teaching method)

የማስተማር ዘዴ ለመማር ማስተማሩ ሒደት በጣም አስፈላጊና አቢይ ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ጥሩ ፍላጎት እንዲኖራቸው ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል፡፡

Evans (1965) መምህሩ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማሳደግ በመማር ማስተማር ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥም በጣም አስፈላጊው ሰው ነው፡፡ ምክንያቱም መምህሩ በሚያስተምርበት ወቅት ለተማሪዎቹ ማነቃቂያ በመስጠት ለትምህርታቸው ንሺ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ የተማሪዎቹ ስሜትም ወደ ሚሰጠው ትምህርት እንዲሆን በማድረግ ረገድ የመምህሩ ማስተማር ዘዴ ከፍተኛ የሆነ እገዛ ደርጋል፡፡ተማሪዎቹ ትምህርቱን ለመማር ትምህርቱን ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል በማለት ይገልፃሉ፡፡

የሰው ልጅ አንድን ትምህርትን ለመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት ካለው ተነሳሽነቱ ከመማር ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡ ፍላጎት ደግሞ ትምህርታዊ ሂደትን እና እንቅስቃሴን ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ እንዲሁም ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ ትክክለኛ የማስተማሪያ መሳሪያን በመጠቀም ማስተማሩ እንደማነቃቂያ ሃይል ከማገልገሉም በተጨማሪ በተማሪዎችም ዘንድ የመማር ፍላጎትን  በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፡፡ ስለዚህም መምህሩ የተማሪዎችን ስብእና እና ፍላጎታቸውን ለይቶ በማወቅ ትክክለኛ የሆነ የማስተማር ስልትን ከትክክለኛ የማስተማሪያ መሳሪያ ጋር በመጠቀም ማስተማር አለበት፡፡ ይህ ተግባራዊ ከሆነ ተማሪዎቹ ለትምህርታቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ወደ ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት ይሸጋገራሉ፡፡

Wilson (1971) እንደሚገልፁት ደግሞ ተማሪዎች አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኙ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ፣ ለትምህርታቸው ፍላጎት እንዲኖራቸው የማስተማሩ ዘዴ ጥሩ እገዛ ያደርጋል፡፡ ብዙ ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት እንደሚገልፁት፣ በሚሰጥ ትምህርት ዙሪያ የመማር ፍላጎት እንዲኖር የምንጠቀመው የማስተማሪያ ዘዴ ትልቅ ሚና ሊጫወት እንደሚችል ነው፡፡ Harmer (1993) በትንሽ  ጥናታዊ ፅሑፍ በማስደገፍ እንደገለፁት የመማር ፍላጎት የሚመጣው ትምህርቱ የሚቀርብበት መንገድ የተስተካከለ ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ የመማር ፍላጎትን ማምጣት፣ የሚቻለውና ስሜትን መቀስቀስ የሚቻለው ትምህርቱ ከቀስቃሽ ማበረታቻ ጋር ተያይዞ የሚሰጥ ከሆነ ነው፡፡ የተማሪውንም የመማር ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፡፡

እንዲሁም Harmer (1991) በ**1970** ባከናወኑት ጥናት የመምህሩን የማስተማር ዘዴን እና በተማሪዎችን የመማር ፍላጎት መሃከል ያለውን ግንኙነት ዘርዘር አድርገው ገልፀዋል፡፡ ጥናቱም

የተካሄደው 12-17 እድሜ ባላቸው ተማሪዎች ላይ ሲሆን ተማሪዎች አንድን መምህር የሚመርጡበትን መስፈርት አስቀምጠዋል፡ ያም በሚከተለው መልክ ከተራ ቁጥር አንድ ጀምሮ እስከ ተራ ቁጥር ዘጠኝ ድረስ ቀርቧል፡፡

1. ትምህርቱን በጣም ሳቢ፣ ማራኪና ተፈላጊ አድጎ የሚያቀርብ
2. በጥሩ ንበት ማስተማር የሚችል
3. ግልፅ አድርጎ መግለፅ የሚችል
4. ቋንቋውን በጥሩ ደረጃ መናገር የሚችል
5. ለተማሪዎቹ ያለው አመለካከት በእኩል ደረጃ ከሆነ
6. ሁሉንም ተማሪ ተሳታፊ የሚያደርግ
7. የችግር ፈቺነት ተግባርን የሚያከናውን
8. ተማሪዎቹ በተግባር እንዲሳተፉ የሚያደርግ እና
9. የመናገር እና የመስማትን የማስተማር ዘዴን ተግባር ላይ የሚያውል ናቸው፡፡

ከላይ በተዘረዘሩት ሀሳቦች መሰረት ከበጣም ከፍተኛ ጀምሮ በተዋረድ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ዝርዝር ተግባሮችን መምህሩ የሚያከናውን ከሆነ ተማሪቹ የትምህርት ፍላጎት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ ከፍሉን ሳቢ እና ማራኪ እንዲሆን ያደርጋል በማለት ይገልፃሉ፡፡

ሌላው በተራ ቁጥር 5,6 እና 9 ላይ የቀረቡት ተግባራት ደግሞ ተማሪዎችን በይበልጥ ተሳታፊ የሚያደርጉና በተማሪውና በመምህሩ የጋራ ግንኙነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዝርዝሩ መሰረት ምንም ትምህርት ያስተምር የመምህሩ ተመራጭነትና ጥሩነት (quality) በቀረበው ሃሳብ ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡

ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪ ለተማሪዎች ሌላ ተጨማሪ ትያቄ ተጠይቀው ያቀረቡት ሃሳና የአንድ መምህር ተመራጭነትና ብቃት በብዙ ዘንድ የሚታወቀው፡፡

1. ለተማሪዎቹ ጥሩ ርህራሄ ሊያሳይ የሚችል
2. ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል ደረጃ የሚመለከት እና
3. በራስ የመተማመን መንፈስ ያለው ናቸው፡፡ እነዚህ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚፈለግ መምህር የሚመረጥበትና ክፍሉን ሳቢና ማራኪ (ተወዳጅ) ማድረግ የሚችል እንደሆነ ተገልፃል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሃሳብ እንደምንረዳው የመምህሩ የማስተማሪያ ዘዴ እየተሰጠ ያለውን ትምህርት ተፈላጊና ተወዳጅ እንዲሆን የራሱ የሆነ አዎንታዊና አሉታዊ ተፅእኖ እንዳለው ነው፡፡

Turi (2003) ከላይ የቀረበውን ሃሳብ በማጠናከር በተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅእኖ የሚያሳድረው የትምህርቱ አቀራረብና የማስተማሪያ ዘዴው ነው ይላሉ፡፡ ይኸውም አንድ ትምህርት ሲቀርብ በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ከሆነ «አዝናኝ» አድርጎ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ትምህርቱን በተማሪዎቹ ዘንድ ተፈላጊና ተወዳጅ ያደርገዋል፡፡ በዚህ አይነት የአቀራረብና የማስተማር ዘዴ የሚቀርብ ትምህርት ተማሪዎችን የሚያዝናና ስለሚሆን ሳይታወቃቸው ትምህርቱን ይማሩታል፡፡ በትምህርቱም ላይ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

በጨዋታ መልክ የሚቀርብ ትምህርት አስደሳች ነው፡፡ ትምህርቱ በጫወታና አዝናኝ በሆነ መልኩ የሚቀርብ ከሆነ ያለ ስልቾት ብዙ መማር ይቻላል፡፡ የተንዛዛና አሰልቺ አይሆንም፡፡ ስለዚህም ይህ የማስተማር ስልት ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት ይጨምራል፡፡

McCombs (1997) Tudor (1996) ገለፃ መሰረት በተማሪ ተኮር በማስተማሪያ ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከፍላጎታቸው ጋር በተገናኘ መልኩ መማር እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በሚማሩት ትምህርት ስለሚደሰቱ፤የመማር ፍላጎታቸውን ከፍ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ዘዴ ትምህርቱ ከእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎት ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ስለሚሰጥ ከተለያየ አቅጣጫ ትምህርቱን ከፍላጎታቸው ጋር አጣጥመው ለመማር ያመቻቸዋል፡፡ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም እንዲችሉም ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ተማሪን ማዕከል ያደረገ ትምህርት፤ ተማሪዎቹ እንደየልምዳቸው ና አስተሳሰባቸው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ በከፍተኛ ፍላጎትና ተነሳሽነት ለትምህርቱ እንዲነቃቁ የማድረግ ሃይል ስላለው፤ ትምርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል፤ ውጤታማም ይሆናሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተለያዩ ሊቃውንት ባቀረቧቸው ገለፃ መሰረት የማስተማሪያ ዘዴውና የትምህርት አቀራረቡ ስልት በተማሪው ፍላጎት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድር መረዳት ይቻላል፡፡

#### 2.4.8.3 የመምህሩ ስብእና

መምህሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት እና ስኬት አስፈላጊና ወሳኝ አካል መሆኑ ቀደም ብሎ በቀረበው ርዕስ ላይ ተነስቷል፡፡ እነዚህ ላይ ደግሞ የመምህሩ ስብህና በማስተማሩ ሂደት ላይ ያለውን ተፅዕኖ ነው፡፡ የመምህሩ የስብእና እና ባህሪ በተማሪው ትምህርት ላይ እና የመማር ፍላጎት ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅእኖን ሊያሳድር ይችላል፡፡ Barnard (1972) እንደሚገለፁት የመምህሩ ስብእና በተማሪው የመማር ልምድና ፍላጎት ላይ ቀጥተኛ የሆነ

ተፅእኖን ሊያሳድር ይችላል ይላሉ:: ይህም የመምህሩ የስብእና ባህሪይ ተማሪው በሚማረው የትምህርት ፍላጎት ላይ ከግምት ሊገባ በሚችል መልኩ ተፅእኖ እንዳሚያሳድር ያስገነዝባሉ::

Evanse (1965) እንደሚሉት ደግሞ የአንድ መምህር አመለካከትና ተግባር የአምባገነንነትንና የአመፀኝነትን ስሜት የሚያንፀባርቅ ከሆነ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተፅእኖና ጫና ስለሚያሳድር በተማሪዎች ላይ የፍራቻ ስሜትን ያነግሳል:: በትምህርታቸው በመማር ፍላጎታቸው ላይም አሉታዊ የሆነ ተፅእኖን ሊያሳድር ይችላል በማለት ይገልፃሉ::

በአንፃሩ ደግሞ መምህሩ የተማሪዎችን ስሜት የሚረዳና፣ ልዩ ድጋፍ የሚያደርግላቸው ከሆነ በተማሪዎቹ ዘንድ ተወዳጅነትን ያተርፋል:: ተማሪዎቹ መምህሩን የሚወዱት ከሆነ ደግሞ የሚያስተምረውን ትምህርትም ሊወዱት ይችላሉ:: በዚህ ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትም ተማሪዎች መምህራቸውን የሚወዱ ከሆነ ለትምህርቱም አዎንታዊ የሆነ አመለካከት የኖራቸዋል:: የማይወዱት ከሆነ ደግሞ በሚማሩት ትምህርት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ስለሚያሳድር ለትምህርቱም አሉታዊ የሆነ አመለካከት ይኖራቸዋል::

ከላይ የቀረበውን ሃሳብ አስመልክተው (ዝኒከማሁ) ማብራሪ ሲሰጡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መምህሩን የሚጠሉት ከሆነ፣ በተለይም ተማሪዎቹ የኮሌጅ ተማሪዎች ከሆኑ፣ መምህሩን በመጥላታቸው ምክንያት የሚማሩትን ትምህርት በማቋረጥ በሚቀጥለው አመት ለመውሰድ ሲሉ ትምህርቱን ላይማሩት ይችላሉ:: በአንፃሩ ግን መምህሩ ሰላማዊ ጠንካራና ከማንኛውም ኢ.ሥን ምግባራዊና ተገቢ ያልሆነ ተግባር ቁጥብ ከሆነ በተማሪዎች ዘንድ መወደድን እና ክበሬታን ስለሚያተርፍ የሚያስተምረው ትምህርትም በተማሪዎቹ ዘንድ ተወዳጅና የተከበረ ያሆናል:: በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ ውጤታማና ስኬታማ ይሆናሉ:: በማለት ይገልፃሉ (Harnard, 1972, Evanse, 1965)::

Harmer (1991) ተማሪዎች መምህራቸውን የሚወዱት ወይም የሚጠሉት ከሆነ በትምህርታቸው ነሺ እና ፍላጎት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል ይላሉ:: ለምሳሌ ያህል ሁለት መምህሮች በተመሳሳይ ዘዴ ተመሳሳይ ተማሪዎችን አስተምረው በሁለቱ መምህሮች የተማሩት ተማሪዎች በመካከላቸው ሰፊ ልዩነት ያለው ውጤት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ:: ከዚህ ማረጋገጥ የሚቻለው መምህሩ እራሱ በትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ እንዳለው ነው:: በአጠቃላይ ከላይ ሊቀውንቱ በገለፁት መሰረት የመምህሩ ስብእና በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖን እንደሚያሳድር ነው- የምሁራኑ ገለፃ የሚያስረዳው::

### 2.4.8.4 የተማሪዎች (አንድን ተግባር ለማከናወን ያላቸው) ተነሳሽነት

እንደ Bugelsk (1971) እና Harmer (1991) አገላለፅ አንድን ተግባር ለማከናወን የሚነሳ ግለሰብ ተግባሩን በቀላል ዘዴ ማከናወን እንዲችል በዙሪያው እውቀት ያስፈልገዋል:: ስለዚህ ተግባሩን ለማከናወን ሊረዳው የሚችል ትምህርትን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያድርበታል:: ለምሳሌ ያህል መኪና የመንዳት ፍላጎት ያለው ሰው መኪናውን ለመንዳት የሚያስችል ትምህርት ለመማር ፍላጎት ያድርበታል:: በሌላ በኩልም አንድ ጉዳይ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ጉዳዩ የሚገኝበትን መንገድና የማግኛ ዘዴውን ለማወቅ በዙሪያው ዕውቀትን የሚሰጥ ትምህርት የመማር ፈላጎት ይኖረል:: እንዲሁም የማንበብ ፍላጎት ያለው ግለሰብ ማንበብ እንዲችልና የማንበብ ችሎታ እንዲኖረው ትምህርቱን ለመማር ፍላጎት ይኖረዋል::

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎችና ሃሳቦች ማየት እንደሚቻለው ለአንድ ተግባር የመነሳሳት ጉዳይ በዙሪያው የተለያዩ እውቀትን እና ችሎታን ለማግኘት ሲባል ትምህርት የመማር ፍላጎት እንዲኖር ግፊት ማድረጉን ነው:: ስለዚህ ትምህርትን ለመማርና አንድን ተግባር ለማከናወን ተነሳሽነት ወሳኝ እንደሆነና የመማር ፍላጎትንም እንደሚጨምር ነው ሊቃውንቱ የሚያስረዱት::

### 2.4.8.5 ተማሪው የሚገኝበት ሁኔታና ማህበራዊ ጉዳይ

በ Tudor (1996)፣ Spoisky (1989) አገላለፅ በተማሪ ፍላጎት ላይ ተፅእኖ ከሚያሳድሩት ውስጥ አንደኛው እራሱ ተማሪው የሚገኝበት ሁኔታ ነው:: ያም ተማሪው ከተማሪው ጋር ያለው ግንኙነት ተማሪው ከተለያዩ የማህበረሰብ አካላትና ከቤተሰብ ጋር ያለው ግንኙነት፣ የአካባቢ ሁኔታ፣ የቤተሰብ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች እና የተማሪው የንቃተ ህሊና ደረጃ በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ ተፅእኖ እንደሚያሳድሩ ይገልፃሉ:: Schonell (1965) ም ከላይ በተረበው ሃሳብ ይስማማሉ::

Schonell (1965) የማንበብና የመማር ፍላጎት በተለያዩ ምክንያቶች ተፅእኖ ሊደርስበት ይችላል:: ከነዛም ውስጥ አንደኛው ምክንያት ከትምህርት ቤት ቁጥጥር ውጭ ያለ ነው:: ትምህርት ቤት የተማሪዎችን የመማር፣ የማንበብ ዝንባሌን እና ፍላጎትን ለማነሳሳት ከፍተኛ ሚና አለው፤ ሆኖም በምንባብና በመማር ፍላጎት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን ጉዳዮች በሚከተለው መልኩ ያቀርባሉ::

እንደ Schonell (1965) ከፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች

1. ቤተሰብ፡- የተማረው ቤተሰብ ተማሪው በሚማረው ትምህርት ላይ የራሳቸውን አስተወፅኦ ያደርጋሉ፡፡ እንዲሁም በተማሪው የመማር ፍላጎት መሰረት ሲሆኑ በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በልጅነት ጊዜ ላይ የሚመጣ አመለካከት መሰረት ሊሆኑ የሚችሉት ቤተሰቦች ናቸው ስለዚህ የልጅነት ጊዜ አመለካከት በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ተፅእኖን ያሳድራል፡፡

2. የተማሪዎች የአእምሮ ችሎታና ንቃተ ህሊና፡- የተማሪው ንቃተ ህሊና የሚገኝበት ደረጃ በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ አሉታዊና አዎንታዊ ተፅእኖን ሊያሳድር ይችላል፡፡ በአእምሮአቸው በሳልና ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎች የመማር ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የመማርና የማንበብ ፍላጎት ከአእምሮ ብስለት እና ንቃተ ህሊና ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡

3. በተፈጥሮ የሚመጣ የመማርና የማንበብ ፍላጎት፡- ተማሪዎች በተፈጥሮአቸው የማንበብና የመማር ፍላጎት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚመጣው ከቤተሰብ የዘር ውርስ ነው፡፡ ስለዚህም አንድ ሰው በተፈጥሮው ለተለያዩ ትምህርቶች የተለያየ ችሎታና ፍላጎት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

4. የማንበብና የመማር ፍላጎት፣ በየጊዜው በሚደረግ ጥረትና ልምምድ ተግባር ሊመጣ ይችላል፡፡ ተማሪው የሚያከናውነው የእለት ተእለት ልምምድ እና ተግባር በተማሪው የማንበብና የመማር ፍላጎት ላይ የራሱ አሉታዊ ተፅእኖን ሊያሳድር ይችላል፡፡

5. አስፈላጊ የሆነን ነገር መርጦ የመማርና የማንበብ ፍላጎት አንድ አስፈላጊ የሆነ ነገር የማንበብና የመማር ፍላጎትን ይጨምራል (Harmer, 1989; Schonell, 1965)፡፡

እንደ Tudor (1996) እና Craig (1979) አገላለፅ ደግሞ በተማሪዎች የመማር ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ተግባራትን በሚከተለው መልኩ ያቀርባሉ፡፡ እነዛም ከተማሪዎቹ ጋር አብረዋቸው የሚማሩት ተማሪዎች ጎበዝ ከሆኑና ከጎበዞቹ ተማሪዎች ለመድረስ የሚጣጣሩ ከሆነ የመማር ፍላጎታቸው እየጨመረና እየዳበረ እንዲሄድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎቹ እርስ በእርሳቸው እየተረዳዱ በጋራ የሚማሩ ከሆነ ተማሪዎቹ ትምህርቱን የመማር ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በእምነት፣ በአመለካከትና፣ በጥቅም በአንድ ቦታ እንዲሰባሰቡ ያደርጋቸዋል (Ball and Davitz, 1970)፡፡

እንደ ምሁራኑም ገለፃ በትምህርት ፍላጎት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ አምስት የስብእና ክፍሎችና ተግባራት ናቸው በማለት፣ አምስቱንም በሚከተለው መልኩ ያስቀምጧቸዋል፡፡

1. የትብብር ሂደት፡- የስሜት ተመሳሳይትን፣ የጋራ ስሜትን እና ፍላጎትን በማሳደግ የጎላ ልዩነትን ማንበብን የሚመለለከት ነው፡፡ ስለጋራ ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ፍላጎትን ይጨምራል፡፡

2. ውድድር፡- ግላዊ ስሜትን እና አመለካከተን የሚጨምር ሲሆን የጋራ አስተሳሰብ ስሜትን ይቀንሳል፤ ቀጥተኛ ተቃርኖን ይጨምራል፤ አንተ መጥፎ ነህ እኔ ጥሩነኝ ወደሚለው አዝማሚያ ይወስዳል፡፡ እና በውደድርም ላይ ከፍተኛ ወደ ሆነ አድሎአዊ ሁኔታ ይጨምራል፡፡ የእስታራቲነትን ተግባር ወደ እኩይ ተግባር ይቀይራል፡፡ የሰውን በጎ አድራጎት እና ተግባራትን ከማሳደግ ይልቅ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖን ያሳድራል፡፡

1. አንዱ ለአንዱ ያለው አመለካከት

ሀ. የመረዳደት ሂደት፤- መተሳሰሰብን፣ መተማመንን እና የሌላውን ስሜት ከመጠበቅ አንፃር ፈቃደኝነት እንዲኖረ ያደርጋል፡፡

ለ. የውድድር ሂደት፡- ተማሪን ወደ ጥርጣሬ፣ የባዕድነት ሥሜትንና የሌላ ሰው ስሜትን እና ፍላጎትን በመጫን እና ከሌላ ሰው ለሚቀርብ ጥያቄ አሉታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

4. የተግባር ዝንባሌ፡- የመረዳዳት ሃደትን ይጨምራል ያለመስማማትን ጉዳይ በጋራ በመሆን እንደ ጋራ ችግር በማየት በጋራ ሆነው እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡ የሌላውን ሰላምና ስሜትን በመጠበቅ ለሚከሰቱ ግጭቶች መፍትሔ የሚሆኑ ጉዳዮችን ወደ መፈለግ ተግባር ይመራል፡፡ የመረዳዳት፣ የመደጋገፍ፣ የመመካከር የመተጋገዝ ፍላጎትን ይጨምራል፡፡ የመግባባት ሥሜትን ይቀንሳል፡፡ ብዙ ሃይል እንዲኖር ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎቹ የሚገኙበት መቸት ወይም ሙድ፣ ተግባር፣ ማህበረሰብ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ የራሱ አስተዋፅኦ እንዳለው ከላይ በዝርዝር የቀረበው ገለፃ ያመለክታል፡፡

## 2.5 የቋንቋ ትምህርት ለመማር በጾታ መሃከል ያለ ፍላጎት ልዩነት

ብዙ ሰዎች በአንድ ነገር ላይ የተለያየ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ እንዲሁም በአንድ ተግባርና ጉዳይ ላይ ደግሞ በተቃራኒው ብዙ ሰዎች አንድ አይነት ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ሰዎች ለአንድ ጉዳይ የጋራ ፍላጎት ሲኖራቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ

የተለያዩ ሰዎች ለተለያዩ ጉዳዮች የተለያየ ፍላጎትና ዝንባሌ እዳላቸው ነው (Schonell (1961). Robinson (2001))::

የሰዎች ፍላጎት የተለያየ እንዲሆን ብዙ ምክንያቶች አሉ:: ከነዛም ውስጥ እድሜና ጾታ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ:: Skinner (1985) በእድሜና በጾታ አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ ፍላጎቶችን Tyler (1955)ን ጠቅሰው ሲገልፁ አንድ ህጻን ልጅ መብራትን አተኩሮ ይመለከትና መብራቱን ለመንካት እንቅስቃሴ ያደርጋል:: ይህ ተግባር ከፍላጎት ጋር የተያያዘ ነው ፍላጎቱም መብራቱን የመንካት ነው:: እንዲሁም ከፍ ከፍ ያሉ ልጆች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ፍላጎት፤ የወንድ ልጅ እድሜ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ይጨምራል:: የሴት ልጅ እድሜ በጨመረ ቁጥር ደግሞ ይቀንሳል:: እንዲሁም የልጆችን ፍላጎት በተለያየ ደረጃ መለካት እንደሚቻል ያመለክታል::

በሌላ በኩልም Tyler (1955) በ15 ልጆች ላይ ባካሄዱት ጥናት ከአምስት አመት ቆይታ በኋላ አራት የልጆች የፍላጎት አይነትን አግኝተዋል:: 1ኛ) ከቤት ውጭ የሚደረጉ ጨወታዎችን 2ኛ) በአሻንጉሊት በግቢ ውስጥ የሚደረግ ጨዋታ 3ኛ) የወረቀትና የእርሳስ ተግባር 4ኛ) አዋቂን በስራ ከመርዳት አንጻር በሴት ልጆችና በወንድ ልጆች መሃከል ልዩነት መኖሩን አረጋግጠዋል:: ሴት ልጆች በአሻንጉሊት መጫወትና ግቢ ውስጥ የሚደረግ ጨዋታን ሲመርጡ፤ወንድ ልጅ ደግሞ ከቤት ውጭ ጨዋታን እና ተግባር መርጠዋል::

Tyler (1955) ባካናወነውም ጥናት ላይ የወንድና የሴት ተማሪዎችን ፍላጎት ከአራተኛ ክፍል ጀምሮ አጥንቷል:: ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ መማርን የሚመርጡት የትምህርት ዘዴ በማየና መጫወት ሲከናወን ነው:: በዚህ ደረጃ በሴትና በወንድ መካከል አንድን ነገር ለመውደድና ለመጥላት ልዩነት አለው:: ልዩነቱም ከፆታ አንፃር በእድሜ ልዩነት የሚመጣ እንደሆነ ነው የሚገልፁት:: በገለፃው መሰረት፤

1. ተማሪዎቹ እያደጉ በሄዱ ቁጥር የተደራጁ ጨዋታዎችን የመጫወት ፍላጎታቸው እየጨመረ ይሄዳል

2. ወንድና ሴት በተመሳሳይ እድሜ ደረጃ የባዉሎጂካል ፍላጎታቸው የጠነከረ ነው

3. ወንድ ልጅ ከ10-12 አመት የወንበዴነት ተግባር የማከናወን ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው:: ልጃገረዶች ደግሞ በይበልጥ የወንበዴነት (gangster) ስሜት የሚኖራቸው በ12 እና በ13 አመት አካባቢ ነው::

4. ወንድ ልጆች ለፕሮፌሽን ስራዎችና ለቴክኒክ ትምህርቶች ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው፣ ሴት ልጆች ደግሞ የጥልፍልፍ ፣ የዲዛይን ስራዎችን መስራትን በተመለከተ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው።

5. ከስርአተ ትምህርት ውስጥ ሥነ-ትምህርታዊ ፍላጎትን በተመለከተ (Caurricular Interset) የወንድ ልጆች ስነ ትምህርታዊ ፍላጎታቸው ሲታይ የተፈጥሮ ሳይንስንና የሂሳብ ትምህርት የመማር ፍላጎት ሲኖራቸው ሴት ተማሪዎች ደግሞ የቋንቋ የእደጥበብ እና የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርትን መማር ይፈልጋሉ።

ከዚህ በላይ በቀረበው መሰረት የተማሪዎች ፍላጎት ከጾታ እና ከእድሜ አንፃር እንደሚለያይ ነው የሚገልፁት። በዚህ ረገድ ብዙ ሊቃውንት እንደሚገልፁት ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ከጾታ አንፃር ሲታይ ይለያያል። አማርኛም በሀገራችን በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚሰጡት የትምህርት አይነት አንዱ ሲሆን ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና አመለካከት ከሁለቱም ጾታዎች አንፃር ሲታይ ሊለያይ ይችላል እንደ ማለት ነው።

ከላይ የቀረበውን ሃሳብ በመደገፍም Hurlock (1980) እንደሚከተለው ማብራሪያ ይሰጣሉ። ወንዶች በክፍል ውስጥ ከሚሰጡት የትምህርት አይነቶች ውስጥ የምንባብን፣ የስነ ጥበብንና፣ ማህበራዊ ሳይንስን የትምህርት አይነቶችን ደብዳቤ ነክ ጉዳዮችን፣ ቋንቋን እና ሥነ- ዕሑፍን በትምህርት ቤት ውስጥ በሚማሩበት ጊዜ የሚሰጧቸው ዋጋ ነው። ስለዚህ ትምህርቶቹን የመማር ፍላጎታቸው አነስተኛ ነው። በሌላ በኩል ለሴት ተማሪዎች ግን ከላይ የቀረቡት የትምህርት አይነቶች ተመራጭና ምቹ ናቸው። ሴቶች ለትምህርቶቹ ከፍተኛ ዋጋ ይሰጧቸዋል። በማለት ገልፀዋል።

Garrison (1965) ፣ Evans (1965) እና Skinner (1985) ከላይ የቀረበውን ሐሳብ በማጠናከር እንደሚገልፁት በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሴት ተማሪዎችና በወንድ ተማሪዎች መካከል አንድን ትምህርት ለመማር የፍላጎት ልዩነት እንዳለ በመግለፅ፣ ሴት ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸውና ወንድ ተማሪዎች ደግሞ ለተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርትና ለሂሳብ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ገልፀዋል።

## 2.6 የትምህርት ውጤት

Blacke (1990) አገላለፅ የትምህርት ውጤት ማለት አንድን የትምህርት አይነት በአላማው መሰረት አስተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ለተማሪዎች በማስተማር፣ ትምህርቱ

ከተሳለፈ በኋላ አላማው ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነና በተማሪዎች ላይ የመጣው የባህሪ ለውጥ ተለክቶ የሚገኝ ውጤት ነው በማለት ይገልፃሉ። በKuhlen (1968) አገላለፅ ደግሞ የትምህርት ውጤት ማለት አላማን መሰረት ያደርገ ትምህርት ለተማሪዎች ካስተማሩ ከተሰጠ በኋላ በተማሪዎች ላይ የመጣው የባህሪ ለውጥ ልኬት ነው። ስለዚህ የትምህርት ውጤት ማለት የባህሪ ለውጥ መጠን ነው በማለት ይገልፃሉ።

ከላይ በቀረበው ገለፃ መሰረት የሁሉም ምሁራን አንድ አይነት ሲሆን ገለፃቸው በአንድ ላይ ሲታይ የትምህርት ውጤት ማለት አንድ ትምህርት ተከናውኖ በተማሪው ላይ የመጣው የባህሪ ለውጥ በፈተና ተለክቶ የሚገኝ እንደሆነ ነው የሚገለፁት።

### 2.6.1 በትምህርት ውጤት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች

Hancock (2004) እና Garry (1970) በተማሪ ውጤት ላይ ተፅእኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች ውስጥ የንሺ ሁኔታ እንደኛው ምክንያት ነው። ንሺ በተማሪ ውጤት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችለው፣ ተማሪው በክፍል ውስጥ ያለው ንሺ ከትምህርቱ አላማ ጋር እንደየ አስፈላጊነቱ ተጣጥሞ ባለመቅረብ የሚመጣ ነው። Skinner (1985) Lewis (1936 & 1942) ጠቅሶ የተማሪዎች ባህሪ፣ ስብእና ፣ ተግባርና የአካባቢ ሁኔታ ወዘተ የመሳሰሉት ጉዳዮችም በተማሪው ውጤት ላይ ተፅእኖ እንደሚያሳድሩ ይገልፃሉ። እነዚህ ምክንያቶች በተማሪው የመማር ፍላጎት ላይ በሚያሳድሩት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ሳቢያ ለትምህርት ውጤትም ላይ አሉታዊና አዎንታዊ የሆነ ተፅእኖን ሊያሳድሩ ይችላሉ በማለት ይገልፃሉ።

#### 2.6.1.1 ተማሪው ለትምህርቱ ያለው ተነሳሽነት

Rubinson (2001) Grdner (1995) ጠቅሶ እና Garry (1970) ሶስት የንሺ ባህሪያት እንዳሉ ይገልፃሉ። እነሱም የግል ጥረት፣ የመንፈስ ጠንካራነት እና ፍላጎት የማሳደር ሃይል ናቸው። ሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት እነዚህ ሶስቱን መሰረታዊና ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው። ተማሪው የሁለተኛ ቋንቋውን እና ለትምህርቱ ተነሳሽ እንዲሆን ከፍተኛ ሃይል ይሰጡታል። ንሺ ውጤትን በማስመዝገብ ዙሪያም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ከተማሪው የመማር ስልት ጋርም ጠንካራ የሆነ ቁርኝት አለው። የትምህርት ስልት ደግሞ አንድን እየተከናወነ ያለን ትምህርት በቀላሉ መረዳት እንዲቻል የሚረዳ ዘዴ ነው። ስለዚህ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ ጥሩ የትምህርት ስልትን በመጠቀም ትምህርቱን ይማራል።ስለዚህም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ለትምህርቱ ትኩረት ለመስጠት ይረዳል።

ንሺ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት የተለያዩ ችግሮችን በመቋቋም ከፍተኛ ውጤትን ለማስመዝገብ ይረዳል በማለት ሲገልፃሉ፤ ተማሪዎች በትምህርታቸው እንዲወድቁ ወይንም ስኬታማ እንዲሆኑ ብዙ ምክንያቶች አሉ:: የተለያዩ ምሁራን በሚገልፁት ገለፃ መሰረት በጣም በተነሳሽ የሆነ ተማሪ ከሌሎቹ ተማሪዎች በተለየ መልኩ ስኬታማ ይሆናል:: ንሺ ውስጣዊ ሃይል ሲሆን አንድን ተግባር እና ትምህርት በአግባቡ ለማከናወን የሚረዳ ውስጣዊ ሃይል ነው:: ስለዚህም ንሺ ካለ እየተካሄደ ባለ ትምህርት ውጤታማ ይሆናል:: ምንም ንሺ ከሌለው ተማሪ ይልቅ በጣም የተነሳሳ ተማሪ ረጅም ግብን ለማሳካት እና ለማከናወን ይችላል:: ስለዚህ አንድ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን ለመልመድ፣ ለማወቅ፣ እና ተምሮ ውጤት ለማስመዝገብ ተነሳሽነት አስፈላጊ ና መሰረታዊ ጉዳይ ነው::

Gardner (2003) Heckhausen (1991)ን ጠቅሶ ንሺ ወደ ግብ የሚያደርስ ባህሪ እንደሆነ ገልፃዋል:: ተነሳሽ ሰው ሃይሉን እና ያለውን ጉልበት በስፋት ይጠቀማል፣ አንድን ተግባር በንቃት ይከታተላል፣ ግብ አለው፣ ዝንባሌው የሰፋ ፣ ፍላጎቱ ምኞቱ ከፍተኛ ተስፋ ያለው ይሆናል:: በስራው ይደሰታል:: ከልብ በመነቃቃት ትክክለኛ ያሆነውን በመጣል የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀም ስኬታማ ይሆናል:: በዚህም ሳቢያ ጥሩ ውጤትን ያስመዘግባል:: ስለዚህም ንሺ፤ በተለይ ውስጣዊ ወይም ውህዳዊ (Intigrative motivation) በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ያደርጋል::

Brown (1993) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን ሲማሩ ከፍላጎታቸው ጋር አዎንታዊ በሆነ መልኩ ግንኙነት ካለው ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ከፍተኛ ንሺ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ንሺ ደግሞ እንደሚታወቀው ከተማዎች ውስጣዊና ውጫዊ ዝንባሌ (Interinsic and exterincic motivation) የሚመጣ እንደሆን ይገልፃሉ:: በአጠቃላይ ንሺ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድር የሚችል ተላውጥ ሲሆን ውስጣዊ ንሺ ከውጫዊ ንሺ የሚበልጥና ተማሪዎቹ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችሉ የሚያደርግ ነው በማለት ይገልፃሉ::

### 2.6.1.2. የማስተማር ዘዴ

እንደ McCombs (1997) ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ የማስተማር ዘዴ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎቹ ከፍተኛ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከመርዳቱም በተጨማሪ በሥርአተ ትምህርት ውስጥም ወደ ግብ የሚያደርስ መንገድን እንዲያውቁ ይረዳል በማለት ሲገልፁ፤ ተማሪን ማዕከል ያደረገ የማስተማር ዘዴ ተማሪው ለትምህርቱ ንሺ እንዲኖረው ስለሚያደርግ ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ይረዳል በማለት ይገልፃሉ::

Tsui (2003) በተግባቦት ዘዴ የሁለተኛ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎቹ ንሺ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ እርስ በእርሳቸው በነፃነት ስለሚማማሩ በትምህርታቸውም የመማር ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በተለይ ተማሪዎቹ ሲማሩ በጫወታ በቀልድ መልክ እየተዝናኑ ቢማሩ ይመረጣል፡፡ በዚህ ሂደት የሚማሩ ከሆነ ትምህርቱን ለመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ስለሚኖራቸው ብዙ ነገሮችን ማወቅ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤትን ማስመዝገብ ይችላሉ በማለት ገለፃቸውን ያቀርባሉ፡፡ ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የመማር ማስተማር ዘዴው በውጤት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳለው ያስረዳል፡፡

## 2.7 ተማሪዎች አንድን ትምህርት ለመማር ያላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ በሚያስመዘግቡት ውጤት መሃከል ያለው ዝምድና

በዚህ የትምህርት ስነ-ልቦና ሊቃውንት በተማሪዎች ውጤትና ተማሪዎቹ ለአንድ ትምህርት ባላቸው ፍላጎት መካከል ያለውን ዝምድና ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥናቶችን እንዳያከናወኑ እና በዚህ ረገድ ብዙ የጥናት ውጤት እንዳገኙ ከሚያቀርቡት ሃሳብ መረዳት ተችሏል፡፡ አንድ አንድ ሊቃውንት ከሚያቀርቡት ሃሳብ በመነሳት ግብ መቺነትና እጥጋቢ ውጤት ካለ ፍላጎት፣ ንሺ እና ዝንባሌ በስተቀር ተግባራዊ እደማይሆን ነው (Grary 1970; ivans 1965 and Bugleski 1971)፡፡

ከላይ የቀረበውን ሃሳብ በመደገፍ Hurlock (1980) እንደገለፁት ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ፍላጎት ከሌላቸው ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ይኸውም ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነትና ትምህርቱን ለማጥናት ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ ይሆናል በማለት ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ በተመለከተ Hurlock በ/1972/ በፃፉት ፅሑፍ ላይ ሲገለፁ አንድ ሰው ለአንድ የትምህርትና ተግባር አነስተኛ ፍላጎት ካለው በትምህርቱ የሚያስዘግበው ውጤትም በጣም ዝቅተኛ ይሆናል የሚል ነው፡፡

ስለዚህ ንቁ የሆኑ ተማሪዎች ለአንድ ትምህርትና ተግባር አነስተኛ ፍላጎት ና ዝንባሌ ካላቸው ተማሪዎቹ በትምህርታቸው የሚያስመዘግቡት ውጤትም አነስተኛና ከተፈለገው በታች እንደሚሆን ነው፡፡ በተጨማሪም ለሚማሩት የትምህርት አይነት የሚመድቡለት የጥናት ጊዜም ውሱንም አነስተኛ እንደሚሆን ያስረዳሉ (Garry, 1970)፡፡

Gardner (2003) የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትና በአምስት ተላውጦዎች ማለትም አመለካከት (Attitude)፣ ውህዳዊ ንሺ (Integrative motivation)፣ ውህዳዊነት (Integratveness) ንሺ (Motivation) እና ውህዳዊ ዝንባሌ (Integrative orientation) በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ላይ የትኛው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፣ በአምስቶቹ

ተላውጦዎች መካከል ያለውን ዝምድና ምን እንደሚመስል ጥናት አከናውነው፤ የተገኘው ውጤት ሁሉም ተላውጦዎች ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር አዎንታዊ ግንኙነት እንዳላቸው፤ ንሺ ደግሞ ከአራቱ ተላውጦ በበለጠ ሁኔታ ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት እንዳለው እና ከእድሜና ከቦታ አንፃር የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ግንኙነት እንደሌለው በጥናታቸው አመልክተዋል::

ከውጤቱም በመነሳት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት፤ ውጤት ለማስመዝገብ ንሺ አቢይና መሰረታዊ ተላውጥ እንደሆነና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ወቅት በተማሪዎች ዘንድ ንሺ እንዲኖራቸው አድርጎ ማስተማር ያስፈልጋል በማለት ሃሳባቸውን ያቀርባሉ::

ከላይ በቀረበው ሃሳብ መሰረት Harmer (1991) እደገለፁት ፍላጎት የንሺ አቢይ ክፍል ነው ይላል ከዚህ ገለፃቸው መረዳት እንደሚቻለው ከላይ Gardner (2003) ያቀረቡትን ውጤት ስንመለከት ፍላጎት ከውጤት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት እንዳለው ያስረዳናል።

Gosh (1990) Herbert (1965) ን ጠቅሶ በፍላጎትና በውጤት መሃከል ከፍተኛ የሆነ የቅርብ ግንኙነት እንዳለው ገልፀዋል:: እንዲሁም Silberman (1972) Schifel (1988) ን ጠቅሶ እንደገለፀው ለመጀመሪያ ጊዜም ሆነ ለመጨረሻ ጊዜ ለትክክለኛ ተግባር ፍላጎትና ንሺ ወሳኝ ጉዳይ ነው:: ፍላጎት ትኩረታችንን ትክክለኛ ወደ ሆነ ተግባር እንድናደርግ ይመራናል:: ተማሪዎችንም ትርጉም ወዳለው ትምህርት ይመራቸዋል:: እንዲሁም ጉዳዩ ሳይረሳ ለረጅም ጊዜ በአእምሮ ውስጥ እንዲቆይ በማድረግና ተጨማሪ እውቀትን እንድንገበይ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል:: አንድን ተግባር ለማከናወን መነቃቃትን ስለሚያመጣ ስራ ወደ ሆነ ተግባር እና ስራ ይመራናል፤ በማለት ይገልፃሉ:: Gardner and Masgoret (2003)፤ Spolsky (1989)፤ Hudsoin (1980)፤ Mackey (1965)፤ Gardner (1968) እና Bugelsk: (1971) ከላይ በቀረበው ሃሳብ ላይ በመስማማት ፍላጎት ለአንድ ክንውን መተግበር እና ለትምህርት ሂደት መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነ የራሳቸውን ገለፃ መሰረት አድርገው ስራ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን ውጤት እና ፍላጎትም ተያያዥ ጉዳዮች እንደሆኑ ይገልፃሉ::

Gosh (1990) ከላይ የቀረበውን ሃሳብ በመደገፍ ሲገልፁ፤ መምህር ትምህርት በሚያስተምርበት ጊዜ የሚሰጠውን ትምህርት ከተማሪዎች የአእምሮ ችሎታ እና ፍላጎት ጋር በማገናዘብ አጣጥሞ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ:: በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ፍላጎት ለውጤታማ ተግባር መሰረት እንደሆነ እና ተማሪዎች ትምህርታቸውን በትጋት እንዲማሩ፤ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችሉ ከማድረግ በሻገር ለመማር-ማስተማሩ ሂደትም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ያስገነዝባሉ::

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ (Design of the study)

በዚህ ክፍል አጠቃላዩ የጥናቱ ዘዴና አከናወን በዝርዝር ይቀርባል፡፡ ጥናቱ የሚከናወነው በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጎሐጽዮን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፣ ገብረ ጉራቻ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ፍቼ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት_ በሚገኙ የ9ኛና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በጥቅሉ ይህ ክፍል የዞኑ ፣ የትምህርት ቤቶቹና የተማሪዎቹ አመራረጥ ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ፣ የጥናቱ አነሂደ ቅደም ተከተልእና የመረጃ አተናተን ምን እንደሚመስል የሚታይበት ነው ፡፡

### 3.1 የዞኖች አመራረጥ

ጥናቱ የተከናወነው በኦሮሚያ ክልል ላይ ነው ፡፡ የኦሃ'ልጸያ ክልል ደግሞ አስራ ስድስት ዞኖች ሲኖሩት ከነዚህ ውስጥ በምክንያታዊ ናሙና መሰረት የሰሜን ሸዋ ዞን ተመርጧል፡፡ የተመረጠበት ምክንያት አጥኝው ከዚህ ዞን በቂ መረጃ፣ በቂ ትብብር እና የሰው ኃይል ማግኘት ስለሚችል ነው ፡፡

### 3.2 የምህርት ቤቶች አመራረጥ

የዚህ ጥናት የተከናወነው በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ከዚህ ዞን ውስጥም የትምህርት ቤት አመራረጥ ዘዴና ስልቱ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ 10 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ ከነዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ሰባቱ (7) ትምህርት ቤቶች የሁለተኛ ደረጃውን እና የመሰናዶውን ትምህርት ቤት በአንድ ላይ አጠቃለው የያዙ ናቸው፡፡ ሦስቱ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የመሰናዶ ትምህርት ቤቱን ሳያጠቃልሉ ከ9ኛ-10ኛ ክፍል ብቻ የያዙ ናቸው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሦስት የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በነሲብ (ዕጣ) ናሙና መሰረት ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም የጎሐጽዮን፣ የገብረጉራቻና የፍቼ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቶቹ በነሲብ

ናሙና የተመረጡበት ምክንያት ለሁሉም ትምህርት ቤቶች እኩል እድል ለመስጠት ታስቦ ነው።

## 3.3. በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ተጠኝዎች (population of the study)

### 3.3.1. ተጠኝዎች (Subject)

በዚህ ጥናት ውስጥ እንዲካተቱ የተመረጡት ተማሪዎች ከሶስቱም ት/ቤቶች ከ9ኛ እና ከ10ኛ ክፍሎች ውስጥ ነው ። በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩት ተማሪዎች 6430 ሲሆኑ ወንድ 4224 ሴት 2206 ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ለጥናት የተወሰዱት በአጠቃላይ 216 ሲሆኑ ወንድ 109 ሴት 107 ተማሪዎች ናቸው። የተመረጡት ተማሪዎችም በምክንያታዊ ንሞና መሠረት በአማርኛ ኢ-አፈፈት የሆኑ ተማሪዎችን ነው።

### 3.3.2 የናሙና አወሳሰድ (Sampling)

ከላይ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ተጠኝዎች ሁለት መቶ አስራ ስድስት (216) መሆናቸው ከላይ ተጠቁሟል። እነኝህ ተጠኝዎች ከጠቅላላ ተማሪዎች ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፈፈት የሆኑትን መሠረት በማድረግ ለአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፈፈት የሆኑትን ብቻ ከገብረጉራቻ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ወንድ 44 ሴት 28 በአጠቃላይ 62 ከጎሐጽዮን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወንድ 32 ሴት 40 በአጠቃላይ 72፣ ከፍቼ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ወንድ 47 ሴት 35 በአጠቃላይ 82 ተማሪዎችን በነሲብ (ዕጣ) ናሙና መሰረት ተመርጠዋል። አጥኝው ነሲብ (ዕጣ) ናሙና የተጠቀመበት ምክንያት ለሁሉም ተጠኝዎች እኩል ዕድል ለመስጠት ታስቦ ነው።

## 3.4 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ (Data gathering method)

### 3.4.1 የጽሑፍ መጠይቅ

የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን በተመለከተ ባለ አምስት የደረጃ ድልድል መለኪያ መስፈንት (five point Likert Rating scale) ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ፍላጎትና አመለካከትን የሚለካ የጽሑፍ መጠይቅ ተዘጋጅቷል። ተማሪዎቹም መጠይቁን በመመሪያው መሰረት እንዲሞሉ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል።

ፍላጎትን የሚለካ መጠይቅ ለማዘጋጀት የተለያዩ ሊቃውንት ያዘጋጁትን የፍላጎት መለኪያ መጠይቆችን ለማየት ተሞክሯል። የዚህን የጥናት የጽሁፍ መጠይቅ ለማዘጋጀትም የBuros (1959,1953)፣ Mitcheil (1985), Callahan (1988) እና Carig (1979) የፍላጎት መለኪያ መጠይቆችን እና ጽንሰ ሃሳቦችን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል። የመጠይቁን የተቀባይነት ደረጃ ለማረጋገጥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሚገኙ የስነልቦና ምሁራን በማሳየት የተቀባይነት ደረጃውን ለማረጋገጥ ተችሏል።

የጽሁፍ መጠይቁን ውስጣዊ እስተማማኝነት (Internal cosistacy of the reliability ) በተመለከተ የክሮንባች አልፋ (Crombach Alpha) የአስተማማኝ መለኪያ ዘዴን በመጠቀም የመጠይቁን አስተማማኝ ደረጃን ለማወቅ ተችሏል። በስሌቱም መሰረት የተገኘው ውጤት 0.79 ነው። ስለዚህ መጠይቁ አስተማማኝ ነው ። በመስክ ጥናት ጊዜ አስተማማኝነቱ ከታወቀ በኋላ ተማሪዎቹ መጠይቁን በመመሪያው መሰረት እንዲሞሉ ተደርጎ መረጃው ተሰብስቧል።

### 3.4.2 የተማሪዎች ውጤት

የተማሪዎችን ውጤት በተመለከተ በየትምህርት ቤቱ ለአንደኛ ወሰነ ትምህርት የሚዘጋጀው አጠቃላይ ፈተና ደረጃውን እና መደበኛነቱን እንዲጠብቅ ለመምህራን ማሳሰቢያ እንዲሰጥ ተደርጓል። በዚሁ መሰረት ፈተናው ከተዘጋጀ በኋላ በየትምህርት ቤቱ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ባሉ መምህራን ፈተናው እንዲታይ ተደርጎ ተገቢነቱ ተረጋግጧል። ከዛም ፈተናው ለተማሪዎቹ ቀርቦ ፈተናው ተከናውኗ ል። የፈተናውን የአስተማማኝ ደረጃውን ለማወቅ ደግሞ ተማሪዎቹ ከተፈተኑ በኋላ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በየክፍል ደረጃው ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡት 20% ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡት 20% የተማሪዎች ናሙና በመውሰድ በፈተናው መሠረት ተማሪዎቹ በመለሱት መልስ መሰረት በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ትንተና ተሰጥቶ ቀርቧል። ከዛም የአስተማማኝ ደረጃውን መለካት እንዲቻል ትንታኔው በአሃዝ ተሠልቶ ከቀረበ በኋላ Kuder Richardson 20 የአስተማማኝነት መለኪያ ሂሳባዊ ስሌት መሰረት ተሰልቶ የአስተማማኝ ደረጃው ተረጋግጧል። የፈተናዎቹ አስተማማኝነትን በተመለከተ የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ነው ። የገብረጉራቻ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል 0.85 ሲሆን የ10ኛ ክፍል ደግሞ 0.83 ነው ። የጎሐጽዮን 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል 0.87 ሲሆን የ10ኛ ክፍል ደግሞ 0.81 ነው ። የፍቼ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል 0.83 ሲሆን የ10ኛ ክፍል 0.89 ነው ። የፈተናው አስተማማኝነት ጠቅለል ባለ

መልኩ ሲታይ በ0.0.8 እና 0.9 መካከል ላይ ነው ። ስለዚህ ፈተናው በከፍተኛ ደረጃ አስተማማኝ ሆኖ ተገኝቷል።

የፈተናው ተቀባይነትና አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኋላ የተማሪዎቹን ውጤት ከየትምህርት ቤቱ ሬከርድ ክፍል እና ከመምህራን የውጤት ማጠራቀሚያ ላይ የአንደኛን መንፈቀ ትምህርት የማጠቃለያውን ፈተና ውጤት ብቻ ተወስዷል። ይህም ሲባል ከ60% ብቻ የተፈተኑትን ነው። ፈተናው ሲወሰድም ከእያንዳንዱ ተማሪዎች የፍላጎት መጠይቅ ጋር በተዛመደ መልኩ ተመዝግቦ ነው። ከዛም የተወሰደው ውጤት ለሂሳብ በሚያመች መልኩ ወደ መቶኛ ተለውጦ በተደራጀ መንገድ ተመዝግቧል።

የትምህርቱ ውጤት ከ60% ያገኙት ውጤት ብቻ የተወሰደበት አብይ ምክንያት ተማሪዎቹ ከ40% የተፈተኗቸውን የፈተናዎች (ቴስቶችን) የአስተማማኝ እና የተቀባይነት ደረጃን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ስለሚሆን በውጤቱ ላይ ችግር እንዳይፈጠር ታስቦ ነው ።

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ (Data analyisis method)

ጥናቱ አሃዛዊ ጥናት ስለሆነ የተሰበሰበው መረጃ ለሂሳብ ስሌት በሚያመች መልኩ ተደራጅቷል። አደረጃጀቱም የተማሪዎቹ የመማር ፍላጎት በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት ከተሰበሰበ በኋላ ተማሪዎቹ ካስመዘገቡት ውጤት ጋር እየተዛመደ ተመዝግቧል። ከዚያም የተማሪዎቹ አጠቃላይ የፍላጎትና የውጤት አማካይ እና መደበኛ ልይት በሂሳብ ስሌት ተሰልቶ ቀርቧል። ከዘያም በፒርሰን የግንኙነት መለኪያ (Pearson correlation) መሰረት በፍላጎትና በውጤት መሃከል ያለውን የግንኙነት ደረጃም ታይቷል። የግንኙነት ደረጃውም 0.76 ሆኖ ተገኝቷል።

በሶስቱ ትምህርት ቤቶች እና በክፍል ደረጃ ያለውን የውጤትና የፍላጎት ልዩነት መኖሩን ለማየት በየርዕስ ጉዳዩ መሰረት በየክፍሉ ለብቻ ለብቻ አማካይና መደበኛ ልይት ተሰልቶ እንዲቀርብ ተደርጓል። ከዛም ከጾታ ከትምህርት ቤት እና ከትምህርት ደረጃ አንፃር ያለውን የአማካዮች ውጤት ልዩነትን ለማወቅ በ "ቲ" ቴስት ቀመር እና (Leveneis test for equalaity of variances) መሰረት ልዩነቶችን ለማየት ተሞክሯል። የ"ቲ" ቴስቱ ውጤት ምክንያታዊ መሆኑን ወይም አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ 0.05 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ በመሆንና በተጠኚዎቹ የደረጃ ነጥብ ላይ በማየት ለማረጋገጥ ተችሏል። ውጤቱን እና እያንዳንዱን ተግባር ለማከናወን የሚያገለግሉ ሂሳባዊ የስሌት መሳሪያዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ።

1. የግንኙነት መለኪያ ቀመር

$$r_{xy} = \frac{N\sum_{xy} - \sum_x \sum_y}{\sqrt{[N\sum_x^2 - (\sum_x)^2]\;[N\sum_y^2 - (\sum_y)^2]}}$$

2. የውጤቱ ከፍተኛ ደረጃን (Significant level) የ «T» ቴስት ቀመርን በመጠቀም ትንታኔ የሚሰጥበት።

$$t = \frac{\bar{X}_1 - \bar{X}_2}{\sqrt{\frac{SD_1^2(n_1 - 1) + SD_2^2(n_2 - 1)}{(n_1 + n_2) - 2}\left(\frac{1}{n_1} + \frac{1}{n_2}\right)}}$$

3. የመጠይቁን አስተማማኝነት ለመለካት የሚያገለግል ቀመር (The reliability of the questionnaire)

$$R_{xx} = \frac{K}{K-1}\left(1 - \frac{\sum (SD)^2}{SD^2}\right)$$

4. r የግንኙነት የአስተማማኝ ደረጃን ለመለካት የሚያገለግል ቀመር

$$t = r\frac{\sqrt{n-2}}{\sqrt{1-r^2}}$$

5. የፈተናውን አስተማማኝነት ለመለካት የሚያገለግል ቀመር

K-R-20 Kuder Richardson estimated

$$r = \frac{K}{K-1}\left\{1 - \frac{\sum pq}{S^2_{xx}}\right\}$$

በአጠቃላይ ከላይ በቀረበው የመረጃ አተናተን ዘዴንና ስሌቶችን በመጠቀም ውጤት ላይ ተደርሷል ከዛም ውጤቱ በሰንጠረዥ ቀርቦ ትንታኔ እና ገለፃ ተሰጥቶበታል። በመጨረሻም ማጠቃለያ እና መደምደሚያ ቀርቦ ውጤቱን መሰረት በማድረግ አስተያየት ሰጥቷል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንታኔና ውጤት

### 4.1 የተጠኝዎች አጠቃላይ ዳራ

#### 4.1.1 ፆታ

በምዕራፍ ሦስት ላይ እንደተገለፀው በናሙናነት የተወሰዱት ተማሪዎች ከኦሮሚያ ክልል ከሰሜን ሸዋ ዞን ከሦስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተውጣጡ ናቸው። ተማሪዎቹም ለአማርኛ ቋንቋ ኢ.አፈፊት ሲሆኑ ከ9ኛ እና ከ10ኛ ክፍል በጠቅላላው 216 በናሙናነት ተወስደዋል። የፆታን ተዋፅኦ ስንመለከት ዛወንዶች 109 (50.5%) እና ሴቶች ደግሞ 107(49.5%) ናቸው።

ሠንጠረዥ አንድ የተማሪዎች የፆታ ስብጥር።

| ፆታ | ጠቅላላ ተማሪዎች | | 9ኛ ክፍል | | 10ኛ ክፍል | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ወንድ | 109 | 50.5 | 50 | 23.15 | 59 | 27.3 |
| ሴት | 107 | 49.5 | 56 | 25.92 | 51 | 23.6 |
| ድምር | 216 | 100% | 106 | 49.07% | 110 | 50.9% |

#### 4.1.2 ዕድሜ ፡-

በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ በናሙናነት የተወሰዱት ተማሪዎች ዕድሜ ሲታይ ዝቅተኛው ዕድሜ 13 ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 29 ነው ። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ከ16-18 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

ሠንጠረዥ ሁለት የተማሪዎችን እድሜ።

| የዕድሜ ክልል | 13-15 | 16-18 | 19-20 | ከ20 በላይ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥር | 9.3% | 159 | 14 | 3 | 216 |
| % | 9.3% | 82.9% | 6.5% | 1.5% | 100% |

### 4.1.3 ከትየምህርት ቤቱ የተወሰዱ ተማሪዎች ስብጥር

ሠንጠረዥ ሦስት፦ ከትምህርት ቤቱ የተወሰዱ ተማሪዎች ስብጥር።

| | የትምህርት ቤት ስም | | | | | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፆታ | ገብረጉራቻ | | ፍቼ | | ጎሐጽዮን | | | |
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁ | % |
| ወንድ | 32 | 14.81 | 41 | 18.98 | 36 | 16.67 | 109 | 50.46 |
| ሴት | 30 | 13.89 | 41 | 18.98 | 36 | 16.67 | 107 | 49.84 |
| ድምር | 62 | 28.7 | 82 | 37.96 | 72 | 33.33 | 216 | 100% |

### 4.1.4 ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚጠቀሙበት ቋንቋ

ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚግባቡበት ቋንቋ የትኛው እንደሆን ተጠይቀው 187(85%) የሚሆኑት ተማሪዎች በቤት ውስጥ የሚገለገሉበት ቋንቋ ኦሮምኛ እንደሆነ ሲገልፁ 29(15%) የሚሆኑት የተማሪዎች ቤተሠብ ደግሞ በኦሮምኛና አማርኛ በእኩል ደረጃ እንደሚጠቀሙ የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል። ሆኖም የሁሉም ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኦሮምኛ ነው።

## 4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና፣

### 4.2.1 በተማሪዎች ትምህርት ውጤትና ለትምህርቱ ባላቸው ፍላጎት መካከል ያለው ግንኙነት።

የዚህ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ያለው ግንኙነትና ዝምድና ለማየት የተከናወነ ትንተና እና ገለፃ ነው። ግንኙነቱን ለማወቅ ተግባር ላይ የዋለው የስሌት ቀመር ፐርሠንት ያዘጋጀው የግንኙነት

መለኪያ (Pearson correlation coefficient) ነው። መለኪያውንም በመጠቀም ተማሪዎች አማርኛን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መሃከል ያለው ዝምድና ታይቷል። ዝምድናውም በስሌቱ መሰረት ተተንትኖ ቀርቧል። ውጤቱም ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ላይ መመልከት ይቻላል።

ሰንጠረዥ አራት፡ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በትምህርቱ ባስመዘገቡት ውጤት መሃከል ያለው ዝምድና።

የግንኙነት ውጤት "r" 0.76

| የተጠኝዎች ቁጥር | የ "t" ቴስት ውጤት | እስጊ ደረጃ "t" ቴስት | አስተማማኝ ደረጃ "p" |
|---|---|---|---|
| 216 | 9.697 | 1.96 | $P<0.05$ |

አምነታዊ አስተማማኝነት "r" [illegible] "≥" ወይም "p" $\leq 0.05$

t = 1.96

ሰንጠረዥ አራት በተማሪዎች የትምህርት ውጤትና ፍላጎት መሃከል ያለው ግንኙነት ወይም ዝምድና የሚያሳይ ነው። ዝምድናውም በግንኙነት መለኪያ ተለክቶ የተገኘው ውጤት "r" = 0.76 ነው። "t" ቴስት ስሌት ተሰልቶ የተገኘው የ"t" ዋጋ ደግሞ 9.697 ነው።

የተገኘው ውጤት አስተማማኝ መሆኑን ስንመለከት የ"t" ቴስት እስጊ ደረጃ (critical value ) በ0.05 አስተማማኝ ደረጃ ላይ በመሆን በ214 የደረጃ ነፃነት ላይ ሲታይ 1.96 ነው። በዚህ መሰረት በስሌት የተገኘው የ"t" ቴስቱ ውጤት ከእስጊ ደረጃው የ"t" ዋጋ በልጦ ተገኝቷል (9.697 >1.96)። እንዲሁም በሁለቱ ተላውጦዎች መሃከል ያለው የግንኙነት ደረጃ የስሌት ውጤት "r" ከእስጊ ደረጃው በልጦ ተገኝቷል (0.76>0.65)። ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በውጤት እና በፍላጎት መሃከል አምንታዊ የሆነ ጠንካራ ግንኙነት እንዳለ ነው።

ከላይ በቀረበው መሰረት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ፍላጎትና በአማርኛ ትምህርት ውጤታቸው መሃከል ያለው ዝምድናና ግንኙነት 0.76 እንደሆነ ተገልጿል። ይህ ግንኙነት እንደ ቦርግስ የግንኙነት ልኬት መሰረት 0.65=.85 መሃከል ላይ ስለመጣ ከፍተኛ የሆነ ዝምድናን አሳይቷል። ከዚህ እንደምንረዳው አማርኛን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤትን ማስመዝገብ እንደሚችሉና በአማርኛ ትምህርት አነስተኛ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ውጤታቸው አነስተኛ እንደሚሆን መረጃው የመለክታል።

ይህ ውጤት ከዚህ በፊት በተጠኑት ጥናቶችና ከተጠቀሱት ሃሳቦች ጋር ተመሳሳይነት አለው ለምሳሌ ያህል Evans (1965)፣ Harlock (1972) እና Buglisk (1971) እንደሚያስረዱት አንድን ትምህርት በመማር ፍላጎትና በውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ የጠበቀ ነው ። ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን ትምህርት የመማር ፍላጎት ካላቸው ሰዓታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ችሎታቸውን፣ እውቀታቸውንና ክሂላቸውን በሙሉ በመጠቀም በትምህርቱ ላይ ስለሚያውሉት ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ግብ መቺ ይሆናሉ በማለት የጎላበት ይህ እንደሚያመለክተው አንድ ተማሪ ለሚማረው ትምህርት ጥሩ ፍላጎት ካለው የሆኑ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችል ነው

በዚህ ጥናት ላይ የተገኘው ውጤትም ሊቃውንቱ ከገለጹት ሃሳብ ጋር ግንኙነት አለው። ምክንያቱም የተማሪዎቹ ውጤት ምንም እንኳ እጅግ ከፍተኛ ባይሆንም ከፍተኛ ፍላጎት የላቸው ተማሪዎች አነስተኛ ፍላጎት ካላቸው ተማሪዎች በተሻለ መልኩ ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውን ነው ውጤቱ የሚያሳየው ።

## 4.2.2 በተማሪዎች ውጤትና ፍላጎት ከፆታ፣ ከትምህርት ቤት እና ከክፍል ደረጃ አንፃር ያለ ልዩነት

### 4.2.2.1 በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል ያለ የትምህርት ውጤት ልዩነት፤

ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያስመዘገቡትን ውጤት በተመለከተ በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል የጎላ ልዩነት አለን? የሚለው ጥያቄ ለመመለስና ለማረጋገጥ የሁለቱንም ፆታ አማካይ ውጤት (Mean) በማነፃፀር የውጤቱን ልዩነት በ <<ቲ>> ቴስት ቀመር መሰረት ተሰልቷል። ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑንም በስሌቱ የተገኘውን ውጤት በማየት የሁለቱን ፆታዎች ውጤት የልዩነት ደረጃ በግልጽ ሰፍሮ የታየበት ነው ።

ሠንጠረዥ አምስት ፡ በሴትና በወንድ ተማሪዎች ውጤት መሃከል ያለ ልዩነት።

| የትምህርት ውጤት ፆታ | አማካይ ውጤት Mean | ማዕከላዊ ልዩነት S.d | የደረጃ ነፃነት df | P"t" ቴስት ውጤት | P"t" ቴስት አስፈላጊ ደረጃ | P "p" ዋጋ አስተማማኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወንድ | 52.14 | 14.5 | 2.4 | 0.903 | 1.96 | P > 0.05 |
| ሴት | 50.43 | 13.25 | | | | |

አስተማማኝ ደረጃ P < 0.05

t > 1.96

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚታየው የወንድ ተማሪዎች አማካይ ውጤት 52.14 ነው፡፡ የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤት 50.43 ነው ፡፡ የወንዶቹ ከሴቶቹ በልጦ ተገኝቷል፡ በሁለቱ አማካይ ውጤት መሃከል ያለው ልዩነት /Mean difference / በ"t" ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ደግሞ 0.903 ነው፡፡ ምክንያታዊ ልዩነቱ በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ242 የደረጃ ነፃነት ላይ የሚገኘው በ"t" ቴስት የአስገ. ደረጃ ዋጋ 1.96 ነው ፡፡ የተገኘው የ"t" ቴስት ቀመር ከዚህ ጋር ሲነፃፀር አንሶ ተገኝቷል፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው በሁለቱ ፆታዎች መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ሲታይ ምክንያታዊ አይደለም፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በሴት ተማሪዎችና በወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ውጤታቸው መሃከል የጎላ ልዩነት አልታየም፡፡ ሌላ ጥናት ካሳየው ውጤት ጋርም ግንኙነት የለውም፡ ለምሳሌ ያህል Hurlock (1965) እና Garrison (1965) ያገኙት ግኝት ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ የቋንቋ ትምህርትን ለመማር ከፍተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ነበር፡ እንዲሁም Skinner (1985) Tyler (1985)ን ጠቅሰው ከወንዶች ይልቅ ሴት ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸውና ትምህርቱም ለሴት ተማሪዎች ምቹ ስለሚሆን ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ የተገኘው ውጤት በወንድና በሴት ተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት ውጤት መሃከል የጎላ ልዩነት እንደሌለ ውጤቱ አመልክቷል፡፡

#### 4.2.2.2 በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር የሚታይ የፍላጎት፣ ልዩነት

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ያላቸውን ፍላጎት በተመለከተ በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል የጎላ ልዩነት አለን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ተሞክሯል፡፡ በዚህም በሁለቱ ፆታዎች በኩል የተማሪዎች የመማር ፍላጎት አማካይ (Mean) በማስላትና በማነፃፀር የውጤቱን ምክንያታዊ ልዩነት "t" ቴስት ቀመር መሰረት ተሰልቶ ተደርጓል፡ ውጤቱ ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ማየት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ ስድስት፦ በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር የፍላጎት ልዩነት

| የትምህርት ዓይነት | ፆታ | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት(s.d) | የደረጃ ነፃነት(d.f) | የ"t"ቴስት ውጤት | የ"t" ቴስት አስጊ ደረጃ | የ"p"ዋጋ ምክንያታዊ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የትምህርት ዓይነት | ወንድ | 75.14 | 13.83 | 214 | 0.459 | 1.96 | P > 0.05 |
| | ሴት | 75.43 | 11.51 | | | | |

ውጤቱ አስተማማኝ የሚሆነው "t" > 1.96

"p" ≤ 0.05

የወንድ ተማሪዎች አማርኛ ለመማር ያላቸው ፍላጎት አማካይ ውጤት 75.14 ነው። የሴቶች ደግሞ 75.43 ነው። በሁለቱ አማካይ ውጤት መሃከል ያለው ልዩነት /mean difference/ በ"t" ቴስት ቀመር ሲሰላ የተገኘው ውጤት 0.459 ነው። ምክንያታዊ ልዩነት በ0.05 ላይ ሲታይ የሚነበበውና ልዩነቱን ሊያሳይ የሚችለው በ242 የደረጃ ነፃነት የሚታየው የ"t" ቴስት የአስጊ ደረጃ እስከ 1.96 ነው ። የተገኘው "t" ቴስት ቀመር ከዚህ ጋር ሲነፃፀር አንሶ ተገኝቷል። ከዚህ አኳያ በሁለቱ ፆታዎች መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ሲታይ ምክንያታዊ ያለመሆኑን ያስረዳል።

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት በሴት ተማሪዎችና በወንድ ተማሪዎች መሃከል አማርኛ ትምህርትን ለመማር ያላቸው ፍላጎት ምንም የጎላ ልዩነት የለውም። ይህ ጥናት ሌሎች በዘርፉ ካጠኑት ጥናት ውጤት ጋርም ግንኙነት የለውም። ለምሳሌ ያህል Hurlock (1965) እና Garrison (1965) ባገኙት ግኝት ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ የቋንቋ ትምህርትን ለመማር ከፍጠኛ ፍላጎት ይኖራቸዋል፣ ከሚለው ሃሳብ ጋር አይገናኝም። ስለዚህ የዚህ ውጤቱ እንደሚያመለክተው በሴትና በወንድ ተማሪዎች መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባለው ፍላጎት መሃከል ምንም የጎላ ልዩነት አልታየም። እንዲሁም Skinner (1995) Tyler (1955) ጠቅሰው ሲገልፁ ወንድ ልጆች ለተፈጥሮ ሳይንስንና ሂሳብን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ሲኖራቸው ሴቶች ደግሞ በቋንቋ ለማህበራዊ ሳይንስና ለእደጥበብ ትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው በማለት የቀረበን የጥናት ውጤት በማስረጃነት ያቀርባሉ። ይሁን እንጂ የተረበው የጥናት ውጤት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት የለውም። ምክንያቱም በወንድና በሴት ተማሪዎች መሃከል የፍላጎት ልዩነት የለም።

## 4.2.3 በትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት፤

### 4.2.3.1 በገብረጉራቻ ትምህርት ቤትና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት፣

በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ካስመዘገቡት ውጤም አንፃር ልዩነት አለን፡ ከትምህርት ቤት አንፃር የውጤት ልዩነት ይኖራል? የሚሉት ጥያቄዎች ለመመለስ በሁለቱ ትምህርት ቤት መሃከል ያለውን የውጤት ልዩነት ለማየት ይቻል ዘንድ በትምህርት ቤቱ ያለውን አማካይ ውጤት (mean ) በማነፃፀር የውጤቱን ልዩነት በ"t" ቴስት ቀመር መሰረት ተሰርቷል። ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑንም በስሌቱ የተገኘውን ውጤት በማየት በሁለቱ ትምህርት ቤቶች ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት በግልጽ ሰፍሮ በማከተለው መልኩ በሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሰባት፡ በገብረጉራቻ ትምህርት ቤትና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነትን

| | ትምህርት ቤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት(s.d) | የደረጃ ነፃነት(d.f) | የ"t"ቴስት ውጤት | የ"t"ቴስት እስጊ ደረጃ | የ"p" ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት | ገብረጉራቻ | 53.1 | 16.35 | 142 | 0.715 | 1.96 | p>0.05 |
| | ፍቼ | 52.22 | 11.932 | | | | |

እስተማማኝ ደረጃ $p<0.05$ "t" $> 1.96$

በሰንጠረዡ ላይ እንደምናየው የገብረጉራቻ ተማሪዎች አማካይ ውጤት 53.1 ሲሆን የፍቼ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከገብረጉራቻ ተማሪዎች ባነሰ መልኩ 52.22 ነው። በሁለቱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት በ"t" ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.715 ነው። ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በ0.05 እስተማማኝ ደረጃ ላይ በመሆን በ144 የደረጃ ነፃነት ላይ ሲታይ የ"t" ቴስት እስጊ ደረጃ 1.96 ነው። የተገኘው የ"t" ቴስቱ ቀመር ከእስጊ ደረጃው የ"t" ቴስት ዋጋ አንሶ ተገኝቷል።

ስለዚህ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በመሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ቢኖረውም ልዩነቱ በስሌቱ መሰረት ምክንያታዊ ሆኖ አልተገኘም።

### 4.2.3.2 በፍቼ እና በጉሐጽዮን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት፤

በሁለቱ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባስመዘገቡት ውጤት መሃከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ለማየት በትምህርት ቤቱ ያለውን የውጤት አማካይ ውጤት(Mean) መደበኛ ልዩነቱም ተሰልቶ ቀርቧል። ከዛም በአማካይ ውጤቱ መሃከል ልዩነት መኖሩን ለማየት የ"t"ቴስት ቀመር ተሰልቶ የቀረበ ሲሆን አጠቃላይ ውጤቱም በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ስምንት፡ በፍቼና በጉሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነትን

| | ትምህርት ቤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት | የደረጃ ነፃነት | የ"t"ቴስት | የ"t"ቴስት እስጊ. | የ"p"ዋጋ አስተማማኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት | ፍቼ | 52.2 | 11.93 | 1152 | 1.703 | 1.96 | p>0.05 |
| | ጉሐጽዮን | 48.69 | 13.46 | | | | |

የአስተማማኝነት ደረጃ $p \leq 0.05$

"t" $\geq 1.96$

በሠንጠረዡ ላይ በቀረበው መሰረት የፍቼ ት/ቤት አማካይ ውጤት 52.2 ነው። የጎሐጽዮን ት/ቤት የውጤት አማካይ 48.69 ነው ። ከዚህ ማየት እንደሚቻለው የፍቼ ትምህርት ቤት አማካይ ውጤት ከጎሐጽዮን ት/ቤት አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል።

በተማሪዎቹ መሃከል ያለውን የአማካይ ውጤት ልዩነት የ"t" ቴስት ውጤት ምክንያታዊነቱን ለማረጋገጥ በ0.05 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ በመሆን በ152 የደረጃ ነፃነት ላይ ሲታይ የ"t" ቴስት እስጊ. ደረጃ 1.96 ነው ። የተገኘው "t" ቴስት በእስጊ. ደረጃ "t" ቴስት ዋጋ አንሶ ተገኝቷል። ከዚህ አንፃር በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሃከል የተገኘው ውጤት ምክንያታዊ ባይሆንም በ0.08 አስተማማኝ ደረጃ ላይ በመሆን በ142 በደረጃ ነፃነት ላይ ሲታይ የ"t" ቴስት እስጊ. ደረጃ ዋጋ 1.64 ነው።

የ"t" ቴስት ውጤት ከእስጊ. ደረጃው "t" ቴስት ውጤት በልጦ ተገኝቷል። ስለዚህ በሁለቱ አማካይ ውጤት መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን የሚለከተል ምክንያቱም 85% አስተማማኝነት አለው። በዚህ ውጤት መሰረት የፍቼ

ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች አማካይ ውጤት በ85% እስተማማኝ ማረጋገጫ ከነሐጽዮን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውጤት በልጦ ተገኝቷል።

### 4.2.3.3 በገብረጉራቻና በነሐጽዮን መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት፡-

በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሃከል በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባስመዘገቡት ውጤት መካከል ያለው ልዩነት በ"ቲ" ቴስት ቀመር ተሰልቶ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ዘጠኝ ፡ በገብረጉራቻና በነሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት

| ትምህርት ቤት / ውጤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት(s.d) | የደረጃ ነፃነት(d.f) | የ"t"ቴስት ውጤት | የ"t"ቴስት እስጊ ደረጃ | የ"p" እስተማማኝ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ገብረጉራቻ | 53.1 | 16.38 | 132 | 1.703 | 1.96 | p>0.05 |
| ነሐጽዮን | 48.69 | 13.49 | | | | |

እስተማማኝ ደረጃ p<0.05 "t" > 1.96

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የገብረጉራቻ አማካይ ውጤት 53.1 ሲሆን የነሐጽዮን ትምህርት ቤት አማካይ ውጤት 48.69 ነው። የገብረጉራቻ ት/ቤት አማካይ ውጤት ከነሐጽዮን አማካይ ውጤት በልጦ ተገኝቷል። በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሃከል ያለወ ልዩነት በ"ቲ" ቴስት ቀመር ሲሰላ የተገኘው ውጤት 1.703 ነው። ልዩነቱ ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ 0.08 የእስተማማኝ ደረጃን መሰረት በማድረግ በ132 የደረጃ ነፃነት ላይ ሰንጠረዥ የ"ቲ" ቴስት ቀመር ከእስጊ ደረጃው "t" ቴስት ዋጋ አንሶ ተገኝቷል።

ስለዚህ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሃከል ያለው አማካይ ውጤት በ0.05 ላይ ሆኖ ሲታይ ልዩነቱ ምክንያታዊ ሆኖ ባይገኝም በ0.1 የእስተማማኝ ደረጃ በ132 የደረጃ ነፃነት ላይ ሰንጠረዥ የ"ቲ" ቴስት እስጊ ደረጃ 1.645 ነው። የተገኘው የ"t" ቴስት ከእስጊ ደረጃው "t" ዋጋ በልጦ ተገኝቷል። ስለዚህ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሃከል ያለው ልዩነት በ0.1 የእስተማማኝ ደረጃ በ132 የደረጃ ነፃነት ሲታይ ምክንያታዊ ልዩነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል። ከውጤቱ መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱ አማካይ ውጤት መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ምክንያታዊነቱ 85% እስተማኝነት እንዳለው ነው። በመሆኑም በገብረጉራቻ

ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች አማካይ ውጤት በ85% አስተማማኝ ማረጋገጫ ከጎሐጽዮን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በልጦ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ በገብረጉራቻና በፍቼ መሃከል ያለው አማካይ ውጤት ሲታይ የገብረጉራቻ በልጦ ቢገኝም ልዩነቱ ምክንያታዊ አለመሆኑን ተረጋግጧል። በፍቼና በጎሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለው አማካይ ውጤት ሲታይ ደግሞ የፍቼ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከጎሐጽዮን ት/ቤት ተማሪዎች በልጦ ተገኝቷል። ልዩነቱ በ0.05 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ ሲታይ ምክንያታዊ ባይሆንም በሌላ በኩል በ0.08 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ ሲታይ ምክንያታዊ ልዩነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል። በተመሳሳይ መልኩም ከገብረጉራቻና በጎሐጽዮን መሃከል ያለው አማካይ ውጤት ሲታይ የገብረጉራቻ ት/ቤት የተማሪ አማካይ ውጤት ከጎሐጽዮን በልጦ ተገኝቷል። የልዩነቱ በ0.05 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ ሲታይ ምክንያታዊ ባይሆንም በ0.1 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ ሲታይ ግን ምክንያታዊ ነው ። ስለዚህ በፍቼና በገብረጉራቻ መሃከል ልዩነቱ የጎላ ባይሆንም ከፍቼና በጎሐጽዮን መሃከል እና በገብረጉራቻና በጎሐጽዮን መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት በ0.1 የአስተማማኝ ደረጃ ላይ ልዩነቱ ምክንያታዊ ሆኖ ታይቷል።

### 4.2.4 በትምህርት ቤት መሃከል ያለ የፍላጎት ልዩነት፣

#### 4.2.4.1 በገብረጉራቻና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር የፍላጎት ልዩነት

በሶስቱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሃከል የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን የፍላጎት ልዩነት ለማየት የተማሪዎች የፍላጎት አማካይ ውጤት ተሰልቷል። የአማካይ ውጤቱን ልዩነት በF ቴስት ቀመር በማስላት ምክንያታዊነቱ መሆኑን ታይቶ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሰረት ተርጎ ትንታኔ ተሰርቶበታል።

ሠንጠረዥ አስር፡- በገብረጉራቻና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የአማርኛ ትምህርት ፍላጎት ልዩነት

| | ትምህርት ቤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት(s.d) | የ"t"ቴስት ውጤት | d.f የነፃነት ደረጃ | የ"t" አስተማማኝ | "p" አስተማማኝ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ገብረጉራቻ | 83.048 | 13.703 | 4.284 | 142 | 1.96 | P<0.05 |
| | ፍቼ | 74.343 | 10.67 | | | | |

አስተማማኝ ደረጃ $p<0.05$ "t" $\geq 1.96$

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የገብረጉራቻ የፍላጎት አማካይ 8301 ነው። የፍቼ ት/ቤት የፍላጎት አማካይ 74.34 ነው። በሁለቱ ት/ቤቶች ፍላጎት መሃከል ያለው የአማካይ የልዩነት ደረጃ በt ቴስት ቀመር ሲሰላ የተገኘው ውጤት 4.28 ነው። ምክንያታዊ ልዩነት በ0.05 ላይ ሲታይና በ142 የደረጃ ነፃነት ላይ የሚነበበው የ"t"ቴስት እስጊ ደረጃ እስከ 1.96 ነው ። እንዲሁም በ0.001 የአስተማማኝ ደረጃ ላይና በ142 የደረጃ ነፃነት ላይ በመሆን የሚነበበው የt ቴስት እስጊ ደረጃ እስከ 3.291 ነው። የተገኘው የ"t"ቴስት ቀመር ውጤት ከሁለቱም የእስጊ ደረጃ t"ቴስት ዋጋ በልጦ ተገኝቷል።

ስለዚህ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በገብረጉራቻና በፍቼ ተማሪዎች መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት 100% አስተማማኝ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የገብረጉራቻ ትቤት ተማሪዎች ከፍቼ ትቤት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን በመማር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

## 4.2.4.2 በፍቼና በጎሐጽዮን መሃከል ያለ የፍላጎት ልዩነት፤

በሁለቱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሃከል የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን የፍላጎት ልዩነት ለማየት የተማሪዎች የፍላጎት አማካይ ውጤት ተሰልቷል። በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን የፍላጎት ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ የሁለቱ ትምህርት ቤት የአማካይ ውጤት በልዩነት ደረጃ በ"t" ቴስት ቀመር ተሰልቶ ውጤቱ በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ <u>አስራ አንድ፦</u> በፍቼና በጎሐጽዮን ትምህርት ቤት መካከል ያለ የአማርኛ ትምህርት ፍላጎትን

| | ትምህርት ቤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት | የደረጃ ነፃነት | የ"t" ቴስት ውጤት | የ"t" ቴስት እስጊ ደረጃ | የ"p" አስተማማኝ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍላጎት | ፍቼ | 74.34 | 10.6912 | 152 | 2.247 | 1.96 | P<0.05 |
| | ጎሐጽዮን | 70.416 | 10.959 | | | | |

አስተማማኝ ደረጃ $p \leq 0.05$ "t" $\geq 1.96$

በሰንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የፍቼ አማካይ ውጤት 74.34 ነው። የጎሐጽዮን የፍላጎት አማካይ 70.416 ነው ። በሁለቱ ትቤቶች የፍላጎት አማካይ ሲታይ የፍቼ ከጎሐጽዮን በልጦ ተገኝቷል የልዩነት ደረጃ የ"t"ቴስት ቀመር ሲሰላ የተገኘው ውጤት 2.244 ነው። በ0.05 ላይ በመሆን በ 152 የደረጃ ነፃነት ለይ ሲታይ የእስጊ ደረጃ የ"t" ዋጋ 1.96 ነው ። የተገኘው የ"t" ቴስት ቀመር ውጤት ከእስጊ ደረጃው "t" ዋጋ በልጦ ተገኝቷል።

ስለዚህ የጥናቱ ውጤት እንደሚታየው በፍቼና በጎሐጽዮን ትምህርት ቤት መካከል ያለው የፍላጎት አማካይ ልዩነት ምክንያታዊ እና አስተማማኝ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የፍቼ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከጎሐጽዮን ትቤት ተማሪዎች የበለጠ የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

### 4.2.4.3 በገብረጉራቻና በጎሐጽዮን መካከል ያለ የፍላጎት ልዩነት፤

በሁለቱ ትምህርት ቤቶች መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን የፍላጎት ልዩነትን ለማየት በሁለቱ ትምህርት ቤት የተገኘው አማካይ ውጤት መደበኛ ልዩነት ተሰልቶ ተገኝቷል ከዛም የሁለቱ ትቤቶች የፍላጎት አማካይ መካከል ያለው ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማየት በ"t"ቴስት ቀመር ተሰልቶ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ <u>አስራ ሁለት፡-</u> በገብረጉራቻና በጎሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለ የውጤት ልዩነትን

| | ትምህርት ቤት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነት | የ"t"ቴስት ቀመር | የነፃነት ደረጃ | የ"t"ቴስት አስጊ ደረጃ | የ"p"ዋጋ አስተማማኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት | ገብረጉራቻ | 83.05 | 13.70 | 5.93 | 131 | 1.96 | $P<0.05$ |
| | ጎሐጽዮን | 70.42 | 10.96 | | | | |

የአስተማማኝነት ደረጃ $p \leq 0.05$

"t" $\geq 1.96$

በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የገብረጉራቻ ትምህርት ቤት የፍላጎት አማካይ ውጤት 83.05 ነው። የጎሐጽዮን ትምህርት ቤት የፍላጎት አማካይ ውጤት 70.416 ነው። ከዚህ እንደሚታየው የገብረጉራቻ አማካይ ውጤት ከጎሐጽዮኑ በልጦ ተገኝቷል። በሁለቱ አማካይ ውጤት መሃከል ያለው ልዩነ በ"t"ቴስት ቀመር ሲሰላ የተገኘው ውጤት 5.93 ነው ። ልዩነቱ አስተማማኝ (ምክንያታዊ) መሆኑን በማረጋገጥ የ"t"ቴስት አስጊ ደረጃ እስከ 1.96 ድረስ ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ የተገኘው የ"t"ቴስት ቀመር ውጤት ከአስጊ ደረጃ "t"ቴስት ዋጋ በልጦ ተገኝቷል።

ስለዚህ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በገብረጉራቻና በጎሐጽዮን ትምህርት ቤት መሃከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ምክንያታዊ (አስተማማኝ) ነው ። በመሆኑም ገብረጉራቻ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከጎሐጽዮን ትምህርት ቤት ተማሪዎች የበለጠ አማርኛ ቋንቋን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

## 4.2.5 በክፍል ደረጃ ያለ የፍላጎትና የውጤት ልዩነት፣

### 4.2.5.1 በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት ፣

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው በ10ኛ እና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መሃከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ለማየት የተማሪዎቹ አማካይ ውጤት ተሰልቶ ቀርቧል። ከዛም በየክፍል ደረጃው አማካይ ውጤታቸውና መደበኛ ልዩነቱ ታይቷል። በሁለቱ የክፍል ደረጃ ያለውን የአማካይ ውጤት ልዩነት ለማየትና አስተማማኝ የሆነ ልዩነት መኖሩን ለማረጋገጥ ደግሞ

የ"t"ቴስት ቀመርም ተግባር ላይ ውሏል። ከዛም የእያንዳንዱ የስሌት ውጤትም በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቦ ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

ሠንጠረዥ <u>አስራ ሰስት</u>፡ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መሃከል ያለ የውጤት ልዩነት

| ውጤት | የክፍል ደረጃ | ቁጥር | አማካይ ውጤት | አማካይ ልይት | "t"ቴስት | የደረጃ ነፃነት | "t"ቴስት አስጊ ደረጃ | "p" አስተማማኝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 9ኛ | 106 | 50.47 | 15.464 | .851 | 214 | 1.96 | P>0.05 |
| | 10ኛ | 110 | 52.08 | 12.196 | | | | |

የአስተማማኝነት ደረጃ "t" ≥1.96

"p" ≤ 0.05

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ማየት እንደሚቻለው የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ውጤት አማካይ ውጤት 50.47 ነው። የሁለቱን አማካይ ውጤት ስናስተያየው የ9ኛ ክፍል አማካይ ውጤት ከ10ኛ ክፍል አማካይ ውጤት አንሶ ተገኝቷል። ስለዚህ በሁለቱ ክፍል መሃከል ልዩነት አለ፡ ልዩነቱን በማየትና ውጤቱ ምክንያታዊና አስተማማኝ መሆኑን ለማየት የ"t"ቴስት ቀመር በተግባር ላይ የዋለ ሲሆን "t"ቴስትም ውጤት 0.851 ነው ። ይህ ውጤት በ0.05 ላይና በ214 የደረጃ ነፃነት ላይ ሲታይ የእስጊ ደረጃው የ"t"ቴስት 1.96 ነው ። የተገኘው የ"t"ቴስት ውጤት ከእስጊ ደረጃው የ"t"ቴስት ዋጋ አንሶ ተገኝቷል።

ስለዚህ በ9ኛ ክፍልና በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት ውጤታቸው መሃከል ምንም የጎላ ልዩነት የላቸውም። በመሆኑም በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች የትምህርት ውጤት ልዩነት የለም።

#### 4.2.5.2 በ9ኛ ክፍልና በ10ኛ ክፍል መሃከል አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያለ የፍላጎት ልዩነት፤

አማርኛ ቋንቋን ለመማር በ9ኛና በ10ኛ ክፍል መሃከል የፍላጎት ልዩነት መኖሩን ለማየት መረጃ ተሰብስቦ የተማሪዎች የፍላጎት አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይት ተሰልቶ ቀርቧል። በሁለቱ የክፍል ደረጃ ያለው የፍላጎት አማካይ መሃከል ልዩነት መኖሩን ለማየትና አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲባል የ"t"ቴስት ቀመር ተግባር ላይ ውሏል ። የእያንዳንዱ መረጃም ተሰልቶ ከቀረበ በኋላ ውጤቱ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ቀርቦ ገለፃ ተሰጥቶበታል።

ሠንጠረዥ እስራ አራት፦ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መሃከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና ልዩነት

| ክፍል | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልዩነ(s.d) | የደረጃ ነፃነት | "ፒ"ቴስት | የ"ፒ"ቴስት እስጊ ደረጃ | "p" አስተማማኝ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9ኛ | 77.59 | 13.02 | 214 | 2.365 | 1.96 | P< 0.05 |
| 10ኛ | 73.55 | 12.143 | | | | |

የአስተማማኝነት ደረጃ "p" ≥ 0.05

"ፒ" ≤ 1.96

ከላይ በሠንጠረዡ ላይ እንደቀረበው የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት 77.59 ነው፡፡ የ10ኛ ክፍል ደግሞ 73.55 ነው፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው የ9ኛ ክፍል የመማር ፍላጎት አማካይ ውጤት ከ10ኛ ክፍል የመማር ውጤት ፍላጎት በልጦ ተገኝቷል ስለዚህ የሁለቱ የክፍል ደረጃ አማካይ ውጤት ልዩነት አለው፡፡ ልዩነቱን ለማየት በ"ፒ"ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 2.365 ነው፡፡

በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ያለው የፍላጎት አማካይ መሃከል ያለው ልዩነት ምክንያታዊ መሆኑን ለማረጋገጥና የተገኘው የ"ፒ"ቴስት ውጤት አስተማማኝ መሆኑን ለማወቅ በ0.05 ላይና በ214 የደረጃ ነፃነት ላይ ሲታይ የእስጊ ደረጃ "ፒ"ቴስት ዋጋ 1.96 ነው፡፡ የተገኘው የ"ፒ"ቴስት ውጤት ከእስጊ ደረጃው "ፒ"ቴስት ዋጋ በልጦ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ማረጋገጥ እንደሚቻለው የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ውጤቱ ያመለክታል፡፡

## 4.2.6 ከትምህርት ቤት አንፃር ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት፤

### 4.2.6.1 በገብረጉራቻ ትምህርት ቤትና በፍቼ ትምህርት ቤት መሃከል ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለው አመለካከት ልዩነት

